# የግብረገብ ትምህርት

# የመምህራን መምሪያ

# አንደኛ ክፍል


## ተርጓሚዎች

ሠለሞን ንጉሴ

አሸብር ሀብታሙ

ፈጠነ ቡልቻ

ጠና ዲሪባ

## አርታዒዎች

ፍቃዱ ታፈሰ

ታሪኩ ነገሰ (ዶ/ር)

## ገምጋሚ

**ደረጀ መኮንን**

## ግራፊክስ

**ታደሰ ድንቁ**

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2015/2023

ይህ የመምህራን መምሪያ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በ2015/2023 ተስማምቶ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው። የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው። ይህን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ በየትኛውም መልኩ ማሳተምም ሆነ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

## ምስጋና

ይህ የመምህራን መምሪያ በትምህርት ሚኒስቴር አመራርት በሀዋሳ ፣ጅማ፣ አዲስ አበባና ባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው፡፡ በመቀጠል በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ቅንጅት ተተርጉሞና ተስማምቶ ተዘጋጀ፡፡

በመሆኑም በዚህ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው የትምህርት ሚኒስቴር፣ የዩኒቨርስቲ አዘጋጆችና በክልላችን ላሉ የትምህርት ባለሙያ ተርጓሚዎችና አስማሚዎች በሙሉ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ላቅ ያለ ምስጋና አለው፡፡

# ማውጫ

መግቢያ ..... v

ምዕራፍ አንድ፡ መልካም ስነምግባር ..... 1

ትምህርት 1: የልጆች ሥነምግባር ..... 2

ትምህርት 2፡ የመልካም ስነምግባር ጥቅም ..... 9

ትምህርት 3፡ ጉዳት ከሚያስከትሉ ድርጊቶች መታቀብ ..... 13

ትምህርት 4. የስነምግባር ማጣት ጉዳቶች ..... 15

ምዕራፍ 2: ቤቴሰብ እና የልጆች ስነ-ምግባር ..... 17

ትምህርት 1: የቤተሰብ አባላት ..... 18

ትምህርት 2: የቤቴሰብ አባላት ድርሻ ..... 20

ትምህርት 3: የቤተሰብ እሴቶች ..... 23

ምዕራፍ 3: ጉርብትና ..... 27

ትምህርት .1: ጎረቤት ..... 28

ትምህርት 2: የጎረቤት አስፈላጊነት ..... 30

ትምህርት 3: ጉርብትናን የሚያጠናክሩ ድርጊቶች ..... 33

ምዕራፍ 4፡ የተማሪዎች ሥነ-ምግባር ..... 36

ትምህርት .1: የመምህራን መዝሙር ..... 37

ትምህርት .2: የተማሪዎች መብት ..... 39

ትምህርት .3: የተማሪዎች ግዴታ ..... 42

ትምህርት .4፡ መልካም ግንኙነት ..... 46

ትምህርት .5፡ መልካም ተሳትፎ ..... 50

ምዕራፍ 5. ባህል ........ 52
ትምህርት .1. ባህላዊ ምግብ ........ 53
ትምህርት . 2. የባህል አልባሳት ........ 55
ትምህርት .3. ባህላዊ ጨዋታ ........ 56
ትምህርት . 4. ባህላዊ እቃዎች ........ 58
ትምህርት .5 የባህል ስርዓቶች ማክበር ........ 60
ምዕራፍ 6. የማህበረሰብ እሴቶች ........ 62
ትምህርት . 1. መረዳዳት ........ 63
ትምህርት .2. መደጋገፍ ........ 65
ትምህርት .3. መዋደድ እና መከባበር ........ 66
ትምህርት .4. እንግዳ መቀበል ........ 68
ትምህርት . 5. የገጠር እና ከተማ የአኗኗር ሁኔታ ........ 69
የ1ኛ ክፍል የግበረገብ ትምህርት ሲለበስ ........ 71

## መግቢያ

ስነ-ምግባር ከሰዎች የለተለት ኑሮ ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ነው፡፡ ዋና አላማውም ዜጎች መልካም ስነ-ምግባር እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡

ይህ የመምህሩ መርጃ በመምህራን የሚተገበሩ ተግባራትን ቀላል እና ውጤታማ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡

በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተካተቱት የክፍል ተግባራት ለመማር ማስተማር በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡

መምህራን የራሳቸው የፈጠራ ችሎታ እንዲሁም በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱትን መመሪያዎች በሚተገብር ከሆነ የመማር ማስተማር ሂደቱ የተሳካና ውጤታማ በማድረግ የትምህርቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ያስችላል፡፡

ይህ የመምህሩ መርጃ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ያካትታል፡ የመማር ማስተማር ስልቶች፤ የተለያዩ ተግባራት እና መልመጃዎች፤ አፈ-ታሪኮች፤ ትካዎች እንዲሁም ክትትል እና ግምገማን ያቀፈ ነው፡፡

## ምዕራፍ አንድ፡ መልካም ስነምግባር

**(20-ክፍለ ግዜ)**

### የምዕራፉ መግቢያ

ይህ ምዕራፍ አራት አብይ የትምህርት ይዘቶች ያቀፈ ነው፡፡ እነሱም: የልጆች ስነ-ምግባር፤ የመልካም ስነምግባር ጥቅም፤ ከጎጂ ድርጊቶች መታቀብ፤ የስነምግባር ማጣት ጉዳቶች ናቸው፡፡

ለሁሉም የትምህርት ይዘቶች የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የትምርትይዘቱን ለማስገንዘብ እንዲረዳ አጫጭር ማስታወሻ እንዲሁም ስዕሎች ተካተዋል፡፡

በተጨማሪም በዚህ መምሪያ ውስጥ የመማር ማስተማር ስልቶች፤ የተማሪዎችን መረዳት የሚያግዙ ማስታወሻዎች፤.እንዲሁም ክትትል እና ግምገማዎች ተካተዋል፡፡

### የመማር ውጤቶች፡

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ፡-

- የልጆች ስነምግባር ምንነት ይረዳሉ፤
- የስነምግባር ጥቅሞችን ያብራራሉ፤
- ከጎጂ ድርጊቶች ይጠነቀቃሉ፤
- ከስነምግባር ጉድለት የሚመጡ ጉዳቶች ይጠነቀቃሉ፡፡

## ትምህርት 1: የልጆች ሥነምግባር

የተሰጠው ክፍለጊዜ (6)

### ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች

ከዚህ የትምህርት ማጠናቀቂያ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የልጆች መልካም ስነምግባርን ይገልጻሉ፤
- የመልካም ስነምግባር  ምሳሌዎችን ይጠቅሳሉ፡፡

ልጆች ምን አይነት ባህሪ ሊኖራቸው ይገባል የሚል የማነቃቂያ ጥያቄን ተማሪዎችን በመጠየቅ የዕለቱን ትምህርት መጀመር ወሳኝ ነው፡፡ በተጨማሪም ልጆች እናት እና አባታቸውን እንዴት ማክበር አለባቸው የሚል ጥያቄን ለተማሪዎች በማቅረብ ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ ከመምህሩ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

በተጨማሪም በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተካተተውን ስዕል ዙሪያ ምን እንደተረዱ ተማሪዎችን በመጠየቅ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ በማድረግ የእለቱን የትምህርት ይዘት መሰረት በማድርግ የተማሪዎችን ግንዛቤ ማስፋት ከመምህሩ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

### ሥዕል፤ እናትና አባትን ማክበር

ይህ ምስል እናት እና አባት ከውጭ ወደ ቤት ሲገቡ ልጆች ከወንበራቸው በመነሳት ክብር ሲያሳዩ፤ በእጆቻቸው የያዙትን እቃ ሲቀበሏቸው እንዲሁም እንዲቀመጡ ወንበር ሲያዘጋጁ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ መልካም ስነምግባር ያላቸው ልጆች ባህሪ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ለቤተሰባቸው ይህን አይነት ስነ-ምግባር እንዲያሳዩ ማበረታታት ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

## አፈ-ታሪክ 1 የአባቱን ምክር በመናቁ የተፀፀተ ልጅ

በዱሮ ጊዜ አንድ ሁለት ልጆች ያሉት ሰውዬ ነበረ፡፡ ከልጆቹ ታናሹ ልጅ ከወላጆቹ ንብረት የድርሻውን እንዲሰጡት ይጠይቃቸዋል፡፡ አባትዮውም ታላቅ እያለ፤ አግብተህ ጎጆ ሳትቀልስ ለምን ይህን ትጠይቃለህ ይህ ከበህላችን ውጪ ነው ብሎ እምቢ አለው፡፡ ልጁም ተናዶ ጦር ይዞ ከቤት ወጥቶ ወደ ሩቅ ገር ሄደ፡፡

በጉዞ ላይ ሳለ ጅብ መጣበት፡፡ አባትዮ ያደረገውን ነገር ሁሉ ለጅቡ ነገረው፡፡ ጅቡም ያዘነለት በማስመሰል፤ ና አብረን እንግባ ከቤተሰቦቼ ጋርም ላስተዋውቀህ አለው፡፡ እየተጓዙም የጅቡ መኖርያ ዋሻ ጋር ሲደርሱ ጦርህን አስቀምጥና ግባ አለው፡፡ ልጁም እሺ ብሎ ጦሩን አስቀምጦ ገባ፡፡ ጅቡም ለቤተሰቦቹ እንድህ አላቸው አይኑን፤ ጆሮውን እና ልቡን አስቀምጡልኝና የቀረውን ብሉ ብሏቸው ሄደ፡፡

ጅቦቹም ደስ ብሏቸው ልጁን ሊበሉት ሲሉ የልጁ አባት እና ወንድም በርቀት ሲከታተሉት ስለነበር ደርሰው ከመበላት አዳኑት፡፡

ልጁም በድንጋጤ ወድቆ ነበርና አባት እና ወንድምየው ተሸክመውት ወደ ቤታቸው ወሰዱት፡፡ ከድንጋጤው ሲነቃ የወላጆቹን ምክር ባለመስማቱ ሊደርስበት የነበረውን አደጋ በመረዳት አባትየው እግር ስር ወድቆ ይቅርታ ጠየቀ፡፡

ልጁን ወስዶት የነበረው ጅብም ከአደን ወደ ዋሻው ሲመለስ አስቀምጡልኝ ያልኳችሁ የልጁ አይን የት አለ አላቸው፤ ቤተሰቦቹም ልጁ አይን ቢኖረው እንዴት ካንተ ጋር ይመጣል አሉት፤ ልቡስ አላቸው፤ ልብ ቢኖረው ጦሩን አስቀምጦ ካንተ ጋር ዋሻ ይገባ ነበር አሉት፤ ከዝያም ጆሮውስ አላቸው፤ ጆሮ ቢኖረው ኖሮ የአባትዮውን ምክር በሰማ ነበር በማለት በልጁ ተግባር ተሳሳቁ ይባላል፡፡

## ክትትልና ም ዘና

- ተማሪዎች ከልጆች ስነምግባር አንዱ የሆነውን እናት እና አባትን ማክበር የሚለውን አስመልክቶ ሀሳብ እንዲሰጡ አድርግ/ጊ

- የተማሪ መማርያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ስዕሎች ማስረዳት ይገባል
- በተማሪ መማሪያ ውስጥ የተካተቱትን ተግባራትን፤ አፈ-ታሪኮችን እና መልመጃዎችን አሰራ/ሪ

ለምሳሌ፤ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ተግባር 1.1 ስር ያለውን ጥያቄ እንዲሰሩ በማድረግ ክትትል አድርግ/ጊ

ተግባር 1.1 ስር መሰጠት ያለበት መልስ

1. በዚህ የእድሜ ደረጃ ልጁ መጠየቅ የማይገባውን ጥያቄ በመጠየቁ መልስ በማጣቱ ተናዶ ከቤት መጥፋቱ
2. ከአባትየው ምክር ይልቅ የጅቡን ምክር መስማቱ ልጁን እንደጎዳው
3. የዚህ አፈታሪክ ዋና ጭብጥ የወላጆችን ምክር አለመስማት ለተለያዩ ጉዳቶች እንደምያጋልጣቸው

መምህራንን ማክበር

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ለመምህራን ያለህን አክብሮት በምን ታሳያለህ የሚለው የማነቃቂያ ጥያቄ ላይ ልጆች ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ካደረክ በኋላ በመጻፉ ውስጥ ያለው ስዕል ምን እንደምያመለክት እንዲናገሩ አበረታታቸው'

***ሥዕል፡ መምህራንን ማክበር***

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ መምህር የመማሪያ ክፍል ሲገባ ከመቀመጫቸው በመነሳት መቀበል እንዳለባቸው፤ በፅሞና ማዳመጥ፤ እጅ በማውጣት ጥያቄ መጠየቅ ወይም መልስ መስጠት እንዳለባቸው ለማሳየት እንዲረዱ ለተማሪዎች ማስረዳት የመምህሩ ተግባር ነው፡፡

## ***ታላቅን ማክበር እና ታናሽን መንከባከብ***

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ታላቅህን በምን መልኩ ታከብራለህ የሚለውን የማነቃቀያ ጥያቄ ׀ተማሪዎች በማቅረብ ሐሳባቸውን እንድያንፀባርቁ በማድረግ

በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ በተሰጠው ምስል በቡድን ተወያይተው የተረዱትን ነገር ለክፍል ተማሪዎች እንዲገልፁ አድርግ/ጊ

ሥዕል፡ **ታላቅን ማክበር እና ታናሽን መንከባከብ**

ይህ ምስል ታናሽ ታላቁን ማክበር እንዳለበት እና ታላቅ ደግሞ ታናሹን መንከባከብ እንዳለበት የሚያሳይ እንደሆነ ለተማሪዎች ማስረዳት ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር መሆኑ መዘንጋት የለበትምል፡፡

መልመጃ 1.1

መምህራንን እና ታላቅን መክበር በተመለከተ በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጠውን መልመጃ እንዲሰሩ እርዳቸው፤ በመጨረሻም ትክክለኛውን መልስ ለተማሪዎች በመንገር ትምህርቱን አጠቃል፡፡

የመልመጃ 1.1 መልስ

1. እውነት 2. እውነት 3. ሐሰት 4. እውነት

**አዛውንቶችን ማክበር**

በዚህ ንሁስ የትምህርት ይዘት ለማቅረብ ይረዳ ዘንድ አዛውንቶችን እንዴት ማክበር አለብን የሚል የማነቃቂያ ጥያቄ ለተማሪዎች በማቅረብ ሁለት ሁለት ሆነው እንዲወያዩ በማድግ አስጀምር/ሪ. በተጨማሪም የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ በሥዕል የተደገፈውን አዛውንቶችን ማክበር ተማሪዎቹ ችንዲረዱ መርዳት ከመምህራን የሚጠበቅ ግዴታ ነው፡፡ ተማሪዎቹም ከስዕሉ በተረዱት መሰረት ቤተሰባቸውን ማክበር እንዳለባቸው፤ ለአዛውንቶች አክብሮት የሚወዱ መሆናቸው፤ አዛውንቶችን ማክበር ደግሞ ምርቃት የሚያስገኝ መሆኑን በአግባቡ እንዲገነዘቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ተግባር 1.2.

**1. አዛውንቶች ምን ይወዳሉ ለሚለው ጥያቄ የሚጠበቅ መልስ**

- አዛውንቶች አክብሮት የሚወዱ መሆናቸውን እንዲጠቅሱ ማበረታታት አስፈላጊ ነው

2. አዛውንቶችን ማክበር ምን ያስገኛል ለሚለው ጥያቄ

- ምርቃት ያስገኛል ብለው እንዲመልሱ ማበረታታት

### የእምነት አባቶችን ማክበር

የእምነት አባቶች በምን መለኩ መከበር አለባቸው የሚል የማነቃቂያ ጥያቄ በማቅረብ ተማሪዎች እንዲሳተፉ አድርግ/ጊ፡፡ለማነቃቂያው ጥያቄ መነሻ የሚሆኑ መልሶች ውስጥ የተወሰኑት፡

- ከመቀመጫ በመነሳት ማስቀመጥ,
- በአክብሮት ማናገር,
- ምክራቸውን መቀበል እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል

በተጨማሪም በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ልጆች የእምነት አባቶችን ማክበር እንደለባቸው፤ቅድሚያ በመስጠት ማስቀመጥ እንዳለባቸው፤ ምራቸውን በመስማት መተግበር እንዳለባቸው ለተማሪዎች ማስረዳት ከመምህሩ ይጠበቃል፡፡

ጓዳኛን ማክበር

ከጓዳኞችህ ጋር ምን ምን አይነት ጨዋታ ትጫወታላችሁ የሚል የማነቃቂያ ጥያቄ በማቅረብ ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲሳተፉ ችንዲሁም መልስ እንዲሰጡ አድርግ/ጊ

### ጠንክሮ መማር

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የጎበዝ ተማሪ ባሪያት የሚሳዩ ሥዕሎች ተቀምጠዋል ተማሪዎቹም እነኚን ስዕሎች በመመልከት ጠንክሮ መማር በምን

እንደሚገለፅ መረዳት እንዲችሉ ታስቦነው፡፡ በመሆኑም መልካም ስነምግባር ያላቸው ልጆች በጊዜ ከእንቅልፋቸው ይነሳሉ፤ የግል ንፅህናቸውን ይጠብቃሉ፤ ልብሳቸውን ባግባቡ ይለብሳሉ፤ ቁርሳቸውን በመመገብ የትምህርት መሳሪያቸውን በመያዝ ወደትምህርት ቤት መሄድ መገለጫቸው ተማሪዎች እንዲረዱ ለማድረግ ታስቦ ስለሆነ እርሶም የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማስፋት እንዲረዳ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

መልመጃ 1.2. በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተሰጠውን መልመጃ ተማሪዎች እንዲተገብሩ አድርግ/ጊ

- ✓ ጠንክሮ መማርን የሚያሳዩ ስዕሎችን እንዲያዛምዱ ሁኔታዎችን አመቻች

ንቁ ተሳትፎ ማድረግ

በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተጠየቀውን የማነቃቂያ ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች መልስ በመስጠት እንዲሳተፉ አድርግ/ጊ፡፡ በተጨማሪም በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተቀመጠው ሥዕል ልጆች የፈጠራ ስራ ውስጥ፤አትክልት በማጠጣት እና አካባቢያቸውን በማፅዳት ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው ለማረግ ታስቦ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች እንደነዚህ ያሉ ተግባራት ላይ መሳተፍ እንዳለባቸው ማስገንዘብ ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

መልመጃ 1.3. የዚህን ትምህርት ይዘት ለማጠቃለል እና ተማሪዎችን ለመገምገም የተዘጋጀ መልመጃ ነው፡ ይህ መልመጃ ስምንት ጠያቄዎችን የያዘ ሲሆን የሁሉም ጥያቄዎች <u>መልስ እውነት መሆኑን</u> የተማሪዎችን ስራ ከገመገምክ/ሽ ቡሃላ ለተማሪዎች ትክክለኛውን መልስ መስጠት አለብህ

የእሉን ትምህርት ለማጠቃለል የሚሰጡ አጫጫር ማስታወሻዎች፡ የልጆች መልካም ስነምግባር መገለጫ የሆኑ አንኩር ነጥቦች፡

- እናት እና አባትን ማክበር፤ እናት ክቡር እንደሆነች፤ አባት አክብሮት እንደሚያስፈልገው

- መምህራንን ማክበር
- ታላቅን ማክበር እና ታናሽን መንከባከብ
- አዛውንቶችን ማክበር፤ ተነስተው መቀበል
- የእምነት አባቶችን ማክበር
- ጠንክረው መማር ወዘተ

**የመማር ማስተማር ስልት**

- ✓ የለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ያቄ መጀመር
- ✓ በተማሪው መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን ማሳተፍ
- ✓ ገለፃ ማድረግ
- ✓ መልመጃዎችን፤ ትረካዎችን እና ተግባራትን ማሰራት

## ትምህርት 2፡ የመልካም ስነምግባር ጥቅም

### ክፍለ-ጊዜ(5)

### ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች

ከዚህ የትምህርት ማጠናቀቂያ በኋላ ተማሪዎች፡-

- መልካም ስነምግባር ያለውን ጠቀሜታ ይጠቅሳሉ፡፡

በተማሪ መማሪያ መጽሀፉ ውስጥ መልካም ስነምግባር ምን ጠቀሜታ አለው የሚለውን የማነቃቂያ ጥያቄ ተማሪዎችን በመጠየቅ የእለቱን ትምህርት ጀምር/ሪ፡፡

### ከአደጋ ይጠብቃል

በተማሪ መማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተጠቀሱትን የቡሹራ እና ሊበን ሥዕል ከዚህ በታች ከተዘረዘረው ትረካ/ንባብ ጋር በማጣጣም የተማሪዎችን ግንዛቤ ማዳበር ያስፈልጋል፡፡

ንባብ/ትረካ፡ ቡሹራ እና ሊበን

ሊበን የአንደኛ ክፍል ተማሪ ነው፤ እህቱ ደግሞ ሦስተኛ ክፍል ነች፡፡ ሊበን እናቱ የምሰጠውን ምክር አይሰማም፡፡ እህቱ ቡሹራ ግን የሚሰጣትን ምክር ትሰማለች፡፡ ሊበን እና ቡሹራ ትምህርት ቤት እስኪደርሱ የመኪና መንገድ ግራቸውን ይዘው እንዲሄዱ፤ መንገድ ላይ ኳስ እንዳይጫወቱ ይነገራቸዋል፡፡ እሺ በማለት ከእናትየው አይን እስኪርቁ ይጠብቁና ሊበን የመኪና መንገድ ላይ ኳስ ይጫወታል፡፡ ቡሹራ ግን ግራዋን ይዛ ነው የምትሄደው፤ ወንድሟ መነገድ ላይ እንዳይጫወት ደጋግማ ብትመከረውም አይሰማትም ። ቡሽራም የወንድሟ□ ድርጊት ለቤተሰባ ትናገራለች ለናትየውም በሊበን ድርጊት እጅግ አዘነች፡፡ ሊበንን በመጥራት መንገድ ላይ ሲሄድ ግራውን እንዲይዝ፤ ከአደጋም እራሱን እንዲጠብቅ መከረችው፡፡እሱም ለጊዜው እሺ ቢልም የመኪና መንገድ ላይ መጫወቱን አላቆመም፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ሎበን መንገድ ላይ ሲጫወት በፍጥነት የሚበር መኪና ገጨው፡፡ በዚህም ምክኒያት ሊበን ትምህርቱን አቁረጠ፡፡ ቡሹራ ግን ከክፍላ አንደኛ በመውጣት ተሠላሚ ሆነች፡፡□

ተግባር 1.3.

1. ከተነበበልህ ትረካ ላይ ምን ተረዳህ ለሚለው ጥያቄ መልስ
   - የቤተሰብን ምክር መስማት ጥቅም እንዳለው
   - የመኪና መንገድ ላይ መጫወት ጉዳት እንደሚያስከትል
   - ምክር መስማት እንደሚያሸልም ወዘተ
2. የመኪና መንገድ ላይ መጫወት ምን ጉዳት ያስከትላል
   - ከአደጋ ይጠብቃል
3. የመኪና መንገድ ላይ ሲሄዱ የቱን መስመር መያዝ አለበት
   - ግራን መስመር በመያዝ መሄድ
   - ይህም ከኣደጋ ይጠብቃል

**ተወዳጅ ያደርጋል**

የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ልጆች ለቤተሰብ አክብሮት መስጠት፤ አዛውንትን ማክበር፤ መምህራንን ማክበር እንዲሁም ጓደኛን መውደድ የሚያሳዩ የተማሪውን ግንዛቤ ለማዳበር ታስቦ የቀረበ ነው፡፡ ስለሆነም ሥዕሎቹን ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ምንባብ፡ ጫልቱ

ጫልቱ የጎሮ ትምህርት ቤት ተማሪ ነች፡፡ ለቤተሰቦችዋ አክብሮት አላት፤የአዛውንቶችን ምክር ትሰማለች፤ መምህራንን እና የክፍል ተማሪዎችን ታከብራለች፤ ከጋደኞቻ ጋር ትግባባለች፡፡ይህ ባህሪዋ በሁሉም እንድትወደድ፤ በትምርቷም ጎበዝ እንድትሆን ረድቷቷል፡፡ በመሆኑም ከክፍላ አንደኛ በመውጣት የአመቱ ተሸላሚ ሆናለቸ ፡፡

ተግባር 1.4.

1. በተማሪው መፅሃፍ ውስጥ ለው ሥዕል ምን ያሳያል
   - መልካም ስነምግባር ስላላት ጫልቱ ያል
2. ጫልቱ ምን አይነት ባህሪ አላት
   - ቤተሰቡዓን የምታከብር
   - የአዛውንቶችን ምክር የምትቀበል
   - መምህራንን የምታከብር

3. ጫልቱ ተወዳጅ ያደረጋት ምንድን ነው
   - መልካም ስነምግባር ስላላት
   - በትምህርቷ ጠንካራ ስለሆነች

ታማኝ ያደርጋል

በዚህ ንዑስ ትምህርት ስር የተቀመጠውን ሥዕል የሰው እቃ አለመውሰድ ፤ ከመሬት የተገኘን እቃ ለባለቤቱ መመለስ ይህም ተወዳጅ እንደሚያደርግ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ለተማሪዎች በሚረዱት አግባብ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

ምንባብ/ትረካ፡ በዳሶ እና ቦንቱ

በዳሶ ታላቅ ሲሆን የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ ቦንቱ ደግሞ ታናሽ ስትሆን የአደኛ ክፍል ተማሪ ነች፡፡ ከእለታት አንድ ቀን በዳሶ እስኪሪብቶ ከመሬት ሲያገኝ የቤተሰቦቹ ምክር ያስታውሳል በመሆኑም ከመሬት ያገኘውን እስኪርብቶ ለመምህሩ ያስረክባል፡፡ መምህሩም በበዳሶ ድርጊት በጣም ይደነቃል፡፡ ቦንቱም ሁለት ጓደኞችዋ ሲጣሉ አይታ ምኒያቱን ስትጠይቃቸው ከመሬት ባገኙት እስኪሪብቶ እንደሚጣሉ አረጋገጠች፡፡ ከዚያም የሚጣሉበትን እስኪሪብቶ በመቀበል ለመምህሯ አስረከበች፡፡መምህሩም እስኪሪብቶውን ለባለቤቱ በመመለስ በቦንቱ ታማኝነት ተደሰተ፡፡ የበዳሶ እህት መሆንዋን በማስታወሱ ታማኝነታቸው ከቤተሰብ የወረሱት መሆኑን በመረዳት አድናቆቱን ገለፀ፡፡

ተግባር 1.5

1. በዳሶ እና ቦንቱ ምን አይነት ስነምግባር አላቸው ለሚለው መልስ
   - ታማኝ ናቸው
   - ያገኙትን እቃ ለባለቤቱ ይመልሳሉ
2. አንተስ የሰው እቃ ከመሬት ብታገኝ ምን ታደርጋለህ ለሚለው ጥያቄ
   - ለማለቤቱ እንዲመለስ አደርጋለሁ ብለው እንዲመልሱ ማበረታታት ያስፈልጋለ

ምርቃት ያስገኛል

በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ መልካም ስነምግባር ያላቸው ልጆችን አዛውንቶች ሲመርቁአቸው የሚሳይ መሆኑን ለተማሪዎች ማስረዳት ተገቢ ነው፡፡

**የተማሪዎችን ግንዛቤ የሚያግዝ ማስታወሻ**

የትምህርት የዘቱን በተመለከተ የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማጠናከር ለተማሪዎች የሚከተሉትን አጫጫር ማስታዎሻ ስጥ/ጪ፡፡ **ለምሳሌ፡**

መልካም ስነምግባር

- ከአደጋ ይጠብቃል
- ተወዳጅ ያደርጋል
- ታማኝ ያደርጋል
- ምርቃት ያስገኛል

**ክትትል እና ግምገማ**

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

**የመማር ማስተማር ስልቶች**

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

# ትምህርት 3፡ ጉዳት ከሚያስከትሉ ድርጊቶች መታቀብ

## የተሰጠ ክፍለ ጊዜ( 5)

## ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች

ከዚህ የትምህርት ማጠናቀቂያ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ ጉዳት የሚያስከትሉ ድርጊቶችን ይሌሉ
- ✓ ጉዳት ከሚያስከትሉ ድርጊቶች መታቀብ አስፈላጊነትን ያውቃሉ

የእለቱን ትምህርት ለመጀመር እንዲረዳ የማነቃቂያ ጥያቄ ጉዳት የሚስከትሉ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ ተማሪዎች እንዲረዱ ማድረግ ከመምህራን የሚጠበቅ ተግበር ነው፡፡

ከዚህ ጥያቄ ውስጥ የሚጠበቅ መልስ፡

- ✓ ስለት ያላቸውን ቁሶች መነካካት መተው
- ✓ እሳት መንካት መተው
- ✓ የመኪና መንገድ ላይ መጫወት መተው
- ✓ እንጨት ላይ መውጣት መተው
- ✓ የኤሌክትሪክ ሽቦ አለመነካካት

ጉዳት ከሚያስከትሉ ድርጊቶች መተቀብን የሚያሳዩ ጨዋታዎች

- ➢ እሳት ምንድ ነው---ሰው ያቃጥላል-- ልንካው-ተው አትንካ
- ➢ ቢላ ምንድ ነው-ሰው ይቆርጣል-ልያዘው-ተው አትያዝ
- ➢ ኤሌክትሪክ ምንድ ነው-ስው ይጎዳል-ልንካው-ተው አትንካ
- ➢ እንጨት ላይ ልውጣ-ሰው ይጥላል-ልውጣ እንዴ- ተው አትውጣ
- ➢ ወንዝ መግባት-ሰው ይወስዳል-ልዋኝ-ተው አትዋኝ
- ➢ ጎርፍ ምንድ ነው-ሰው ይወስዳል-ልግባበት-ተው አትግባ
- ➢ ውሻ ምን ያደርጋል-ሰው ይነክሳል-ልያዘው-ተው ይቅርብህ
- ➢ አህያ ምን ያደርጋል-ሰው ይረግጣል-ስሩ ልግባ- ተው አትግባ

ተግባር 1.6. ጉዳት የሚስከትሉ ተግባራትን አዛምድ

ጉዳት የሚያስከትሉ ተግባራትን ተማሪዎች ሁለት ሁለት ሆነው እንዲጫወቱ አድርግ

መልመጃ 1.4. መልስ---- 1. ረ 2.ሠ 3.መ 4.ሐ 5.ለ 6.ሀ

# ትምህርት 4. የስነምግባር ማጣት ጉዳቶች

የተሰጠው ክፍለ ጊዜ-4

## ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች

ከዚህ የትምህርት ማጠናቀቂያ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ ስነምግባር በማጣት የሚመጣን ችግርን ይዘረዝራሉ

የስነምግባር ማጣትን አስመልክቶ የማነቃቂያ ጥያቄ በተማሪዎች መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ስነምግባር ማጣት ምነ ጉዳት ያስከትላል በሚለው ላይ ተማሪዎችን በመጋበዝ እንዲወያዩ ማድረግ አስፈላጊ ነው

ንባብ/ትረካ፤ አቶ ነገዎ እና ልጆቹ

አቶ ነገዎ ቢራ እና ሂንሰርሙ የሚባሉ ልጆች አሉት፡፡ቢራ የቤተሰቡን ትእዛዝ ያከብራል፤ ሀቀኛ ነው፤ ቤተሰቡንም ያከብራል፡፡ሂንሰርሙ ግን ስነምግባር የለውም፤ውሽታም ነው፤ ቤተሰቡንም አያከብርም፤ስራም አይወድም፡፡አባታቸውም ቢራ ጥሩ ስነምግባር ስላለው በመመረቅ ስጦታም ሰጡት፡፡ ሂንሰርሙ ግን ስለሚዋሽ ምርቃትም ስጦታም አልተሰጠውም፡፡

ተግባር 1.7.

1. ቢራ ለምን ተሸለመ ለሚለው መልስ
    - መልካም ስነምግባር ስላለው
    - ትዕዛዝ ስለሚቀበል
    - እውነት ስለሚናገር
2. ሂንሰርሙ ለምን ተቆጨ

- ስነምግባር በማጣት ስጦታ ስለተከለከለ

3. ከዚህ ትረካ ምን ተረዳህ ለሚለው

መልካም ስነምግባር አስፈላጊ መሆኑን፤ስነምግባር ማጣት ግን ለተለያዩ ችግሮች የሚያጋልጥ መሆኑን ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ይህን ትረካ ክፍል ውስጥ ለተማሪዎች በማንበብ በትረካው ውስጥ ያሉትን ባሪያት በመረዳት ከራሳቸው ባህሪ ጋር እንዲያመዛዝኑ መርዳት የመምህሩ ድርሻ ነው፡፡

## የተማሪዎችን ግንዛቤ የሚጨምሩ አጫጭር ማስታዎሻዎች ስጥ

ለምሳሌ፡ ስነምግባር ማጣት፡

የአካል ጉዳት ያስከትላል

ለቅጣት ይዳርጋል

ቤተሰብ እንዲያዝንብን ያደርጋል

ብቸኝነትን ያስከትላል

## ክትትል እና ግምገማ

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

## የመማር ማስተማር ስልቶች

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት 5.እውነት

# ምዕራፍ 2: ቤቴሰብ እና የልጆች ስነ-ምግባር

## የተሰጠ ክፍለ ጊዜ፡ 19

### *የምዕራፉ መግቢያ*

ይህ ምዕራፍ ሦስት አብይ የትምህርት ይዘቶች ያቀፈ ነው፡፡ እነሱም: የቤተሰብ አባላት፤ የቤተሰብ አባላት ድርሻ፤ እና የቤተሰብ እሴቶች ናቸው፡፡ ለሁሉም የትምህርት ይዘቶች የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የትምርትይዘቱን ለማስገንዘብ እንዲረዳ አጫጭር ማስታወሻ እንዲሁም ስዕሎች ተካተዋል፡፡

በተጨማሪም በዚህ መምሪያ ውስጥ የመማር ማስተማር ስልቶች፤ የተማሪዎችን መረዳት የሚያግዙ ማስታወሻዎች፤. እንዲሁም ክትትል እና ግምገማዎች ተካተዋል፡፡

### *የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:*

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የቤተሰብ አባላትን ይዘረዝራሉ፤
- የቤተሰብ አባለትን ድርሻ ይገልፃሉ፤
- የቤተሰብን እሴትን ያደንቃሉ፡፡

## ትምህርት 1: የቤተሰብ አባላት

### የተሰጠ ክፍለ ጊዜ፡ 5

ዝቅተኛ የሚጠበቅ የመማር ክህሎት፤-

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- ✓ የቤተሰብን ምንነት ይገልፃሉ፤
- ✓ የቤተሰብ አባላት ይዘረዝራሉ፡፡.

ይህን ትምህርት ከመጀመርህ/ሽ በፊት የቤተሰብ አባላት እነማን ናቸዉ የሚለዉን የማነቃቂያ ጥያቄ ተማሪዎች እንዲመልሱ አመቻችላቸዉ'

በእለቱ ትምህርት ውስጥ መነሳት ያለባቸው ነጥቦች የቤተሰብ አባላት እናት፤አባት፤ልጆች፤ ሃያት እና የመሳሰሉት ያጠቃልላል፡፡

ሥዕል፡ የቤተሰብ አባላት

በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ የቤተሰብ አባላት እነማን እንደሆኑ የሚያሳይ ሥዕል ተማሪዎች እንዲረዱት ታስቦ ስለሆነ የቤተሰብ አባላት የደም ትስስር ያላቸው ሰዎችን እንዲሁም ሌሎችን ያካትታል፡፡

ቤተሰብ ማለት በጋራ የሚኖሩ የስጋ ዝምድና ያላቸዉ ሰዎች እና ሌሎችንም ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

ለምሳሌ፡

- ➢ ወላጆች፤ እናት እና አባት
- ➢ ልጆች፤ ወንድም እና እህት
- ➢ አያቶች፤ የሴት አያት እና የወንድ አያት

- ሌሎች ዘመዶች እና የመሳሰሉትን ልያካትት ይችላል'

**መዝሙር፡ የቤተሰብ ፍቅር**

- ✓ እኔ እናቴን  ወዳታለሁ፡
- ✓ እኔ አባቴን እወደዋለሁ፡
- ✓ ምክራቸውን እሰማለሁ፤
- ✓ እኔ ወንደሞቼን እወዳለሁ፡
- ✓ ምክራቸውን እቀበላለው፤
- ✓ እኔ እህቴን ወዳታለሁ
- ✓ እንክብካቤዎን አደንቃለሁ
- ✓ እኔ ሃያቴን አከብራታለው
- ✓ ምክርና ምርቃቷን እወዳለሁ

## ትምህርት 2: የቤቴሰብ አባላት ድርሻ

የተሰጠ ክፍለጊዜ፡ 5

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ክህሎት፤-

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- ✓ የቤተሰብ አባላትን የስራ ድርሻ ይገልፃሉ

የቤተሰብ አባላትን በተመለከተ ቤተሰቦችህ ምን ምን የስራ ድርሻ አላቸው የሚለውን የማነቃቂያ ጥያቄ ተማሪዎች እንዲመልሱ አበረታታቸዉ፡፡

ሥዕል፡ የቤተስብ አባላት ድርሻ

በተማሪው መማርያ መፅሃፍ ውስጥ ቤተሰብ የተለያዩ የስራ ድርሻ ያላቸው መሆኑን ለማሳየት ታስቦ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ልጆቻቸውንበፍቅር መንከባከብ፤ልብስ መግዛት፤ሰውነታቸውን ማጠብ፤ምግብ መስጠት እንዲሁም ትምህርት ማስጠናት ወዘተ በመጥቀስ ተማሪዎችን ማስጨበጥ ያፈልጋል፡፡

መልመጃ 2.1.

በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ያለውን የእናት እና አባት ሥዕል ከተሰጠው ጥያቄ ጋር አዛምድ፡፡ የዚህ አዛምድ መልስ- 1. ሐ 2. መ 3. ለ 4.ሀ

ሥዕል፡የልጆች ድርሻ

በተማሪው መፅሃፍ ውስጥ የልጆች ድርሻ ተማሪዎች እንዲረዱት አድርግ፡፡ ይህም ሥዕል ልጆች ንፅህናቸውን መጠበቅ፤ቤተሰባቸውን በስራ መርዳት፤ማጥናት እና ወዘተ ለማስረዳት የተዘጋጀ ስለሆነ ተማሪዎችን ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

**ተግባር 2.2.**

1. **ልጆች ምን ድርሻ አላቸው ለሚለው**

   - ንፅህናቸውን መጠበቅ፤
   - ቤተሰባቸውን በስራ መርዳት፤
   - ማጥናት
   - እቃ ማጠብ
   - ቤት ማፅዳት

2. አንተ ምን ምን ድርሻ አለክ ለሚለው

   - መብት መጠበቅ
   - ውሃ መቅዳት
   - መልዕክት መላክ ወዘተ እንዲመልሱ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

3. ጥናት ማጥናት የማን ድርሻ ነው ለሚለው

   - ማጥናት የተማሪ ድርሻ ነው ብለው እንዲመልሱ መደረግ አለበት

## የትምህርቱ አጫጭር ማስታወሻ

## የእናት እና አባት ድርሻ

- ✓ ልጆችን መንከባከብ
- ✓ ምግብ መስጠት
- ✓ ማስጠናት
- ✓ ሁኔታዎችን ማመጫቸች

## የልጆች ድርሻ፤

- ✓ ንፅህናቸዉን መጠበቅ፤ ፊት መታጠብ፣እግር  መታጠብ፣
- ✓ ቤተሰቦቻቸዉን ማገዝ፣
- ✓ በአግባቡ ማጥናት፣
- ✓ ለበቴሰብ ክብር መስጠት፣
- ✓ ታላላቆቻቸዉን ማክበር፣
- ✓ መታዘዝ፤ እጅ ማስታጠብ፣ መላክ፣
- ✓ እፅዋቶችን ዉሃ ማጠጣት እና ወዘተ'

## ትምህርት 3: የቤተሰብ እሴቶች

የተሰጠው ክፍለ ጊዜ፡ 5

የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ክህሎት፤-

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የቤቴሰብ እሴቶችን ያብራራሉ

ለበተሰብህ/ሽ ያለህን/ሽን ፍቅር እንዴት ትገልጻለህ/ሽ? የሚለዉን የማነቃቂያ ጥያቄ ላይ ተማሪዎች ሀሳባቸዉን እንዲሰጡ ሁኔታዎችን አመቻችላቸዉ፡፡

***ሥዕል፡ የቤተሰብ ፍቅር***

የተማሪው መማረሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቤተሰብ ፍቅር የሚያሳይ ሥዕል ተማሪዎች እንዲረዱ እርዱአቸው፡፡ይህም ልጆች ለቤተሰባቸው ፍቅር እንዲኖራቸው ታስቦ ነው በመሆኑም ልጆች ቤተሰባቸውን መውደድ፤ጎረቤታቸውን እንዲሁም ጓደኛቸውን መውደድ እንዳለባቸው ማስረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

***ሥዕል፡ መረዳዳት-***

የተማሪው መማረሪያ መፅሃፍ ውስጥ መረዳዳትን የሚያሳይ ሥዕል ተማሪዎችን ለማስገንዘብ ታስቦ ነው፡፡ ይህም ልጆች እናት እና አባታቸውን ቤት በማፅዳት፤ እጅ በማስታጠብ፤ በመሳሰሉት መርዳት እንዳለባቸው ለማሳየት ታስቦ ነው፡፡

***ሥዕል፡ ፈርሃ እግዝአብሔር***

የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ስለሦስት ሰዎች ከፈሪሃ እግዚአብሄር ጋር የተያያዘ አፈታሪክ ተማሪዎች እንዲረዱ ማገዝ ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

አፈ-ታሪክ፡**ፈርሃ እግዝአብሔር**

በድሮ ጊዜ ሦስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ነበሩ፡፡ አንዱ አይነ-ስዉር፣ ሁለተኛዉ ሽባ፣ ሦስተኛዉ ደግሞ ደሃ ነዉ፡፡ ለችግሮቻቸዉ መፍትሄ ፍለጋ ፈጣሪ ጋ ሄዱ፡፡ ሦስቱም ችግሮቻቸዉን ተናገሩ' ፈጣሪም ችግራቸዉን በመረዳት ወደ ቤታችሁ ሂዱ ነገ ጠዋት ለዉጡን ታያላቹ፤ያያቹትንም ለዉጥ መጥታቹሁ ንገሩኝ አላቸዉ፡፡ አይነስዉሩ አይኑ ማየት፤ ሽባዉም መራመድ ቻሉ' ለደሃዉም ላሙ ወለደችለት፡፡ ነገር ግን አየነስዉሩ እና ሽባዉ በደምብ አልዳንም ብለው ፈጣሪን ዋሹ' ደሃዉ ሰዉዬ ግን እዉነቱን ብቻ ተናገረ::

ፈጣሪም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ቤታችሁ ሂዱና ነጌ ጠዋት ለዉጡን ታያላችሁ አላቸዉ' ያዩት ለዉጥም፤ አይነስዉሩ መልሶ ታወረ፤ ሽባዉም እንደበፊቱ ሆነ፡፡ ደሃ የነበረዉ ግን እዉነት ስለ ተናገረ ሀብታም ሆነ ይባላል፡፡

**ተግባር 2.3.**

1. ከሦስቱ ሰዎች ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለው የቱ ነው ለሚለው
   - ድሃው ስውዮ መሆኑን ተማሪዎችን ማስገንዘብ ያስፈልጋለ
2. እግዚአብሄርን ማሞኘት ይቻላል ለሚለው
   - ከተነበበው አፈታሪክ እንዲረዱ ተማሪዎቹ በማድረግ እግዚአብሄርን ማሞኘት እንደማይቻል ማስገንዘብ ያፈልጋል
3. ከተነበብልህ አፈታሪክ ምን ተረዳህ ለሚለው
   - ትዛዝን ማክበር አስፈላጊ መሆኑን
   - እግዚአብሄርን አለመፍራት ጉዳት እንዳለው ብለው መመለስ አለባቸው

**የቤተሰብን ንብረት መጠበቅ-** እያንዳንዱ የቤተሰብ አባላት የቤተሰቡን ንብረት ከጉዳት መጠበቅ ይጠበቅባቸዋል'

**የቤተሰብ የኑሮ/እኮኖሚ ሁኔታ መረዳት-**ሁሉም የቤተሰብ አባላት የቤተሰቡን የኑሮ ደረጀ አዉቆ ከአቅም በላይ የሆኑ ጥያቄዎችን አለመጠየቅ ተገቢ ነዉ' መልካም ስነምግባር ያላቸዉ ልጆች ወላጆቻቸዉ የማይችሉትን ነገር እንዲገዙላቸዉ ማስቸገር እንደሌሌባቸው ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ትረካ፡ የአቶ ቱምሳ ቤተሰብ

አቶ ቱምሳ ኩለኒ እና ያደታ የተባሉ ልጆች አላቸዉ:: ልጆቹም በቤተሰባቸዉ ኑሮ በጣም ደስተኞች ናቸዉ:: ወላጆቹም እንደ አቅማቸዉ መጠን ለልጆቻቸዉ ደብተር፣ እስክርብቶ፣ ልብስ፣ ጫማ እና ቦርሳ ይገዙላቸዋል:: ልጆቹም የቤተሰባቸዉን የኑሮ ሁኔታ ስለሚያዉቁ፤ከቤተሰብ አቅም በላይ የሆነ ጥያቄ በመጠየቅ ወላጆቻቸዉን አያስቸግሩም፡፡'

ተግባር 2.4.

1. የአቶ ቱምሳ ልጆች የቤተሰባቸውን የኑሮ ሁኔታ የተረዱ ናቸው ለሚለው፡
   - መምህር/ት ይህን ትረካ ለልጆቹ በማንበብ ልጆች የቤተሰቦቻቸዉን የኑሮ ሁኔታ እንዲረዱና ከወላጅ አቅም በላይ ጥያቄ እንዳይጠይቁ ማስገንዘብ አለብህ/ሽ::
2. እናንተስ የቤተሰባችሁን የኑሮ ሁኔታ ትረዳላችሁ ለሚለው
   - በትረካው ውስጥ ያለውን ገፀ ባህሪያት በተማሪዎቹ በመጋባት ልጆች የቤተሰባቸውን የኑሮ ሁኔታ የተረዱ መሆን እንዳለባቸው ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

## የመማር ማስተማር ስልቶች

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

| የምዕራፍ የክለሳ መልስ |
|---|
| **I. እዉነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ/ሽ**<br>**1.** እዉነት 2. እዉነት 3. እዉነት 4. እዉነት 5. እዉነት |
| II. ምርጫ<br>1. ሐ 2. ሀ 3. ሀ 4. ሐ |

## ምዕራፍ 3: ጉርብትና

## የተሰጠ ክፍለ ጊዜ:19

### *የምዕራፉ መግቢያ*

ይህ ምዕራፍ ሦስት አብይ የትምህርት ይዘቶች ያቀፈ ነው፡፡ እነሱም: ጎረቤት፤ የጉርብትና አስፈላጊነት፤ ጉርብትናን የሚያጠነክሩ ድርጊቶች ናቸው፡፡

ለሁሉም የትምህርት ይዘቶች የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የትምርትይዘቱን ለማስገንዘብ እንዲረዳ አጫጭር ማስታወሻ እንዲሁም ስዕሎች ተካተዋል፡፡

በተጨማሪም በዚህ መምሪያ ውስጥ የመማር ማስተማር ስልቶች፤ የተማሪዎችን መረዳት የሚያግዙ ማስታወሻዎች፤.እንዲሁም ክትትል እና ግምገማዎች ተካተዋል፡፡

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- ✓ የጉርብትና ባህርያትን ይገልጻሉ፤
- ✓ የመልካም ጉርብትና አስፈላጊነት ያብራራሉ፤
- ✓ ጉርብትናን የሚያጠናክሩ ድርጊቶች ይዘረዝራሉ::

## ትምህርት .1: ጎረቤት
## የተሰጠ ክፍለጊዜ:6

የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት፡-

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የጎረቤትን ትርጉም ይገልጻሉ
- የጉርብትና ምንነትን ያቃሉ፡፡

ይህን ትምህርት ለመጀመር የሚረዳ ልጆች ከጎረቤታቸው ጋር ምን አይነት ጨዋታን ይጫወታሉ የሚል  የማነቃቂያ ጥያቄ ላይ ተማሪዎች ሀሳባቸዉን እንዲሰጡ መርዳት ከመምህር ይጠበቃል፡፡ ተማሪዎቹ በመልሳቸው ልጆች እንደ ኩዋስ፤ገመድ መዝለል፤ስኞ ማክሰኞ እና የመሳሰሉትን እንደሚጫወቱ እንዲመልሱ ማገዝ አስፈላጊ ነው፡፡

ሥዕል፡ ጎረቤት የሚያሳይ

በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ጎረቤት ስላምታ መጠያየቅ፤ ልጆች ደግሞ የተለያዩ ጨዋታዎችን አብረው መጫውት እንዳለባቸው ተማሪዎችን ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም እነዚህን ጨዋታዎች ተማሪዎች በየተራ እንዲጫወቱ አድርግ/ጊ፡፡

ድርጊት 3.1.

1. በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተዘረዘሩትን ጨዋታዎች ተማሪዎች የሚወቁትን እንዲነግሩ ታስቦ የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም ሥእሎቹን በማስገንዘብ የሚያውቁትን ጨዋታ እንዲነግሩ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ሌላ የሚያወቁት የጫወታ አይነት ካለ እንዲጠቅሱ አድርግ/ጊ
2. የሚከተለውን ተረት በቡድን እንዲጫወቱ አድርግ/ጊ

   ተረት-ተረት

ተያቂ----------ተረትተረት ጠጠያቂ------ቀጥል

ተጠያቂ--------የመሰረት ጠያቂ---------ወይፈን

ጠያቂ---------ሚስት ተጠያቂ -------ቀጥል

ተጠያቂ-------ቀጥል ጠያቂ---------ጊደር

ጠያቂ---------ባል ተጠያቂ--------ቀጥል

ተጠያቂ------ቀጥል ጠያቂ---------ጊደር

ጠያቂ--------ወይፈን

ማሳሰቢያ፡ **ወይፈን**- ወንድ ልጅን፤ **ጊደር** ደግሞ ሴት ልጅን ያሳያል

ጠያቂው እወቅልኝ በማለት ይጤቃል፤ ተጠያቂው ካወቀ የእን እከሌ ቤት ይላል ካላወቀ አትስደበኝ በማለት መልሱን እንዲነግረው ያደርጋል

## ከመልካም ጎረቤት ባህርያት መካከል ጥቂቶቹ፤

- ✓ በሀዘን እና በደስታ አብሮ መሆን
- ✓ መከባበር
- ✓ በሰላም አብሮ መኖር
- ✓ አለመረባበሽ
- ✓ አከባቢን በጋራ ማፅዳት
- ✓ መረዳዳት

## ትምህርት 2: የጎረቤት አስፈላጊነት

**የተሰጠ ክፍለጊዜ: 7**

የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት፤-

ከዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የጉርብትናን አስፈላጊነት ይገልፃሉ

  የዕለቱን ትምህርት ለመጀመር ይረዳ ዘንድ ስለ ጉርብትና አስፈላጊነት ከዚህ በታች  የተቀመጠውን አባባል ተማሪዎቹን አወያያቸዉ'

  ተረት

ጎረቤቴ ደህና ይደር እኔ ደህና እንዳድር'

ከሩቅ ዘመድ ይልቅ የቅርቡ ጎረቤት ይሻላል' መልእክቱ የጉርብትናን ወሳኝነት የሚያሳይ እንደሆነ በቂ ማብራርያ ስጥ/ጪ፡፡

ሥዕል፡ የጉርብትና አስፈላጊነት

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ጎረቤት ቡና አብሮ በመጠጣት፤በመረዳዳት፤ልጆች ደግሞ አብረው ትምህርት ቤት አብረው በመሄድ ይገለፃል፡፡ ስለሆነም እኚህን ሥዕሎች ተማሪዎች እንዲረዱ መርዳት የመምህሩ ግዴታ ነው፡፡

ትረካ፡ አቶ መርጋ እና ቶላ

አቶ መርጋ እና አቶ ቶላ  ጎረቤታሞች ናቸዉ፡፡ አቶ መርጋ ሀብታም ሲሆን አቶ ቶላ ግን ደሃ ነዉ፡፡ እነኝህ ጎረቤታሞች ተለያይተዉ አያዉቁም፤ እንደ አንድ ቤተሰብ በአንድነት ይኖራሉ፡፡ ልጆቻቸዉም አብረው ይማራሉ፤ አብረው ይጫወታሉ፤ ይዋደዳሉ፤ይረዳዳሉ፤ይከባበራሉ፡፡ በመሆኑም እኚህ ሁለት ቤተሰቦች መልካም ጉርብትና እና ግንኙነት አላቸዉ፡፡

ተግባር 3.2.

የአቶ መርጋ እና አቶ ቶላ መልካም ጉርብትና የሚያሳየውን ምንባብ ለተማሪዎቹ አምብብ/ቢ፤

1. አቶ ቶላ እና አቶ መርጋ ምን አይነት ጉርብትና እንዳላቸው ተማሪዎችን አወያይ
2. ልጆቻቸው ያላቸውን ቀረቤታም እስረዳ
3. በተጨማሪም ተማሪዎች ከጎረቤት ልጆች ጋር ምን አይነት ግንኙነት እንዳላቸው እንዲገልፁ አድርግ/ጊ

መልመጃ 3.1.

በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ለውን አዛምድ ተማሪዎች እንዲሰሩ አድርግ

መልስ- 1. ሐ 2. መ 3. ሀ 4. ለ

ቀጥሎ የተዘረዘሩት የጉርብትና ባህርያት ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ስጥ/ጪ፡፡

- ደስታን አብሮ መካፈል፤
- በሃዘን ጊዜ መረዳዳት
- የተጣሉትን ማስታረቅ
- በደቦ/በጅጊ በጋራ መስራት
- አብሮ መጫወት
- መረጃ መለዋወጥ
- ኢቃ መዋዋስ
- መመካከር እና ወዘተ፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

## የመማር ማስተማር ስልቶች

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

## ትምህርት 3: ጉርብትናን የሚያጠናክሩ ድርጊቶች

**የተሰጠ ክፍለጊዜ:6**

የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት፤-

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- ጉርብትናን የሚያጠናክሩ ድርጊቶች ይለያሉ

የእለቱን ትምህርቱ ከመጀመርህ በፊት ጉርብትናን የሚያጠናክሩ ድርጊቶች ምንምን ናቸዉ? የሚለዉን የማነቃቂያ ጥያቄ ላይ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡበት አድርግ/ጊ፡፡ በተጨማሪም ጉርብትናን የሚያጨናክሩ ድርቶች ምን ምን እንደሀኑ በቡድን አወያይ፡፡

ሥዕል፡ የጅብ እና አንበሳ ጉርብትና

የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ እርጉዝ ላም ያለው ጅብ እና በሬ ያለው አንበሳ ጉርብትና ለማሳየት የቀረበ ሥዕል ነው፡፡ይህም ስዕል አንበሳው እና ጅቡ እንዴት ይኖሩ እንደነበረ ለምን እንደተጣሉ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን አፈ-ታሪክ ለተማሪዎች በማንበብ የተማሪዎችን ግንዛቤ ማዳበር አስፈላጊ ነው፡፡

አፈ-ታሪክ፡ አንበሳ እና ጅብ

በድሮ ጊዜ አንበሳ እና ጅብ በጉርብትና አብረው ይኖሩ ነበር። አንበሳ በሬ ነበረው ጅብ ደግሞ እርጉዝ ላም ነበረችው፡፡ ከብቶታቸዉንም በተራ ይጠብቁ ነበር፡፡ ከዕለታት ባንድ ቀን የአንበሳ ተራ በሆበት ቀን የጅቡ ላም ወለደች:: ይሁንና አንበሳ ወለደው የሱ በሬ እንደሆነ በማስመሰል ጥጃዉን መዉሰድ ፈለገ፡፡ ይህን ለማድረግም እንዲረዳው የላሚቷን የእንግዴ ልጅ በመዉሰድ የበሬዉ ጭራ ላይ በማሰር ጥጃዉን ወስዶ ወደ ቤቱ ገባ፡፡

ጅቡም የወለደችው የኔ ላም ናት በማለቱ ከአንበሳ ጋር ተጣሉ፡፡ ሁለቱም ጉዳያቸዉን በሽምግልና ለመፍታት አውሬዎችን በሙሉ ሽምገልና ጠሩ፡፡ የመጡትም አውሬዎቹ

በሙሉ ስለፈሩ ለአንበሳ ፈረዱ፡፡ በመጨረሻ ጦጣ ዘግይታ በመምጣቷ ሽምግናዬን ንቀሽ ነዉ የዘገየሽዉ በማለት አንበሳ ተቆጣት፡፡ ጦጢትም ሽምግልናህን ንቄ ሳይሆን መሬት ተቀዶ ስሰፋ ነበር አለችው፡፡ አንበሳም መሬት ከመች ወዲህ ነዉ መቀደድ የጀመረዉ ብሎ አፈጠጠባት:: ጦጢትም ከመቼ ወዲህ ነዉ በሬ መዉለድ የጀመረዉ ብላ ለጅብ ፈርዳ ዘላ ዛፍ ለይ ወጣች ይባላል፡፡

<u>የዚህ አፈ-ታሪክ ቁምነገር</u>

አንበሳው በሱ ተራ ቀን ታማኝነቱን በማጉደል የራሱ ያልሆነውን ነገር
የኔ ነው ማለቱ እና
ጉልበቱን ተማምኖ ሽማግሌዎችን አስፈራርቶ በውሸት አስፈረደ፡፡
ሌሎቹ አዉሬዎች አንበሳውን ፈርተው በውሸት ፈረዱለት። ጦጢት
ብልጠቷን ተጠቅማ የተደበቀውን እውነት ገልጣ ትክክለኛ ውሳኔ
ሰጠች። ይህ የአንበሳ ድርጊት የጅብ እና የአንበሳን ጉርብትና
ጎድቶታል፡፡

ተግባር 3.3

1. አንበሳው እና ጅቡ ለምን ተጣሉ ለሚለው
   - አንበሳ ጉልበቱን ተማምኖ የጅቡን ጥጃ ለመውሰድ በመሞከሩ
   - መተማመን በማጣታቸው
2. ጥፋቱ የአንበሳ ወይስ የጅቡ ነው ለሚለው
   - በተነበበላቸው አፈታሪክ ላይ በማተኮር ጥፋቱ የአንበሳ እንደሆነ እንዲመልሱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
3. ተማሪዎች ከዚህ አፈ-ታሪክ ላይ የመተማመንን አስፈላጊነት እንዲሁም ጉልበትን በመጠቀም ፍላጎትን ለማሟላት መሞከር ጉርብትናን እንደሚጎዳ ማስረዳት የመምህራን ግዴታ ነው፡፡

ግንዛቤን የሚጨምሩ ማስታወሻ

ጉርብትናን የሚያጠናክሩ ድርጊቶች ውስጥ ጥቂቱ፡

- እዉነት መናገር
- መዋደድ
- መተማመን
- መረዳዳት
- መከባበር
- መመካከር እና ወዘተ መጥቀስ ያስፈልጋል፡፡

| የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄ መልስ |
|---|
| 1.እዉነት 2. እዉነት 3. እዉነት 4. እዉነት 5.እዉነት 6. እዉነት |

## ምዕራፍ 4፡ የተማሪዎች ሥነ-ምግባር

### የተሰጠ ክፍለ ጊዜ:18

#### የምዕራፉ መግቢያ

ይህ ምዕራፍ አምስት አብይ የትምህርት ይዘቶች ያቀፈ ነው፡፡ እነሱም: የመምህራን መዘሙር፤ የተማሪዎች መብት፤የተማሪዎች ግዴታ፤ መልካም ግንኙነት እና መልካም ተሳትፎ ናቸው፡፡ ለሁሉም የትምህርት ይዘቶች የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የትምርትይዘቱን ለማስገንዘብ እንዲረዳ አጫጭር ማስታወሻ እንዲሁም ስዕሎች ተካተዋል፡፡

በተጨማሪም በዚህ መምሪያ ውስጥ የመማር ማስተማር ስልቶች፤ የተማሪዎችን መረዳት የሚያግዙ ማስታወሻዎች፤. እንዲሁም ክትትል እና ግምገማዎች ተካተዋል፡፡

#### የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የተማሪዎች ሥነምግባር  ምንነት ይገልጻሉ፤
- መምህራኖችን ያከብራሉ፤
- የተማሪዎች መብት እና ግዴታ ይዘረዝራሉ፤
- የመልካም ግንኘነት ጥቅምን ይገልጻሉ፤
- የተሳትፎን አስፈላጊነት ይረዳሉ፡፡

## ትምህርት .1: የመምህራን መዝሙር

(ክፍለጊዜ: 3)

የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት፡-

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የመምህራንን ክብር የሚያሳይ መዝሙር ይዘምራሉ፡፡

ከዚህ ትምህርት ጋር ተያይዞ በተማሪዎች መፅሐፍ ዉስጥ ለመምህራኖችህ ያለህን ክብር እንዴት ትገልፃለህ የሚለውን የማነቃቂያ ጥያቄ ተማሪዎች ተራ በተራ ሀሳብ እንዲሰጡበት እድል በመስጠት የእለቱን ትምህርት መጀመር ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም፤ተማሪዎች ስለ መምህራን ክብር የተዘጋጀዉን መዝሙር እንዲዘምሩ ማመቻቸት ከመምህራን የሚተበቅ ግዴታ ነው፡፡

ሥዕል፡ የመምህራን ክብር

በተማሪዎች መፅሐፍ ዉስጥ የመምህራንን ክብር የሚያሳዩ ሥዕሎች ተቀምጠዋል፡፡በመሆኑም ተማሪዎች ይህን ሥዕል እንዲረዱት እና ግንዛቤያቸውን ማጠንከር ይገባል፡፡

መዝሙር፡

<u>የመምህርን ክብር የሚገልፅ መዝሙር</u>

| | |
|---|---|
| እንጨት ረጅም ረጅም | የማህበረሰብ መብራት |
| ረጅም እንደ ሰማይ | የጨለማን ጥምጣም |
| አበባ ቁረጪልኝ | አንተ ነህ ምታበራው |
| ለመምህሬ ላድርስ | ምስጋናህ አልቅም |
| መምህር የዕውቀት ምንጭ | ታሪክህ ያወሳሃል |

ተግባር.4.1.

የመምህራንን ክብር የሚያሳይ መዝሙር ለተማሪዎች በማንበብ የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በቡድን እንዲሰሩ አድርግ/ጊ

1. ለመምህራችሁ ያላቹን ፍቅር በመዝሙር ገላፃችሁ ታወቃላችሁ ለሚለው
   - ተማሪዎች መዝሙሩን እንዲዘምሩ አበረታቷቸው
2. የመምህርን ክብር የሚገልፅ መዝሙር ተማሪዎች በቡድን እንዲዘምሩ በማድረግ አስፈላጊውን ሁኔታ አመቻች

የዚህ ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመጨመር የሚከተሉትን አጫጭር ማስታዎሻዎች ስጥ፡፡

- መምህራንን ማካበር
- ለመምህራን ያላቸውን ፍቅር በመዝሙር መግለፅ
- የመምህራንን ምክር  መተግበር እና ወዘተ

## ትምህርት .2: የተማሪዎች መብት

(ክፍለግዜ: 3)

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ክህሎት፤-

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የተማሪዎችን መብት ይዘረዝራሉ::

የእለቱን ትምህርት በጥያቄ መልክ ለመጀመር ክፍል ውስት ጥያቄ ትመልሳለህ? ተማሪዎች ምን ምን መብቶች አላቸው?የሚል የማነቃቂያ ጥያቄ ተጠይቁል፡፡ በነዚህ ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች በመሳተፍ ሃሳብ እንዲሰጡ መርዳት ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

***ሥዕል፡ የመማር መብት***

በተማሪዎች መፅፍ ውስጥ የተቀመጠውን የመማር መብት የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመጨመር ታስቦ ስለሆነ የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመጨመር ይረዳል፡፡

ተግባር 4.1.

ተማሪዎች የመማሪያ መፅሃፍ አላችሁ የሚለውን ጥያቄ እንዲመልሱ በማድረግ መፅሃፍ ናግኘት የተማሪ መብት መሆኑን ለተማሪዎች ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

ትረካ፡ ደራርቱ እና ሮባ

ደራርቱ እና ሮባ የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸዉ፡፡ ደራርቱ በጊዜ በትምህርት ገበታዋ ላይ ትገኛለች፡፡ ሮባ ግን አርፍዶ ይመጣል:: ደራርቱ መምህራኖች የሚጠይቋትን ጥያቄ ትመልሳለች:: ያልገባትን ነገር ጓደኞቿን ትጠይቃለች፤ ጓደኞቿ ያቃታቸዉን መምህራኖችን ትጠይቃለች:: ደራርቱ በፈተና ቀን እራሷን ችላ ፈተና ትሰራለች፤ ሮባ ግን የጥያቄዎችን መልስ ስለማያዉቅ ከሌሎች ተማሪዎች ለመኮረጅ

ይሞክራል፡፡በዚህም ምክኒያት ደራርቱ ከክፍሏ አንደኛ በመዉጣት ስትሸለም፤' ሮባ ግን ወደ ቀጣይ ክፍል ባለማለፉ እያለቀሰ ወደ ቤቱ ገባ፡፡ፈተና መኮረጅ የትምህርት ስረዓትን መጣስ ነዉ፡፡

ተግባር 4.2.

ስለደራርቱ እና ሮባ የቀለበውን ትረካ በማንበብ የሚከተሉትን ጥያቄ እንዲሰሩ አድርግ/ጊ

1. ከተነበበልህ ትረካ ምን ተረዳህ ለሚለው በትረካው መሰረት እንዲመልሱ መርዳት ከመምህራን ይጠበቃል
2. ሮባ ባህሪ ምን ይመስላል

ሥዕል፡ ጥያቄ የመጠየቅ መብት

በተማሪዎች መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ጥያቄ የመጠየቅ መብት ዙሪያ የቀረበውን ሥዕል ተማሪዎችን እንረዱት ማብራሪያ ከሰጠህ ቡሃላ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት እንዲወያዩ አድርግ፡፡ ለምሳሌ፡የተሰማቸውን ስሜት መናገር፤ ያለገባቸውን መጠየቅ ችና መልስ የማግኘት መብት እንዳላቸው ማስገንዘብ ያፈልጋል፡፡

ተግባር 4.3.

በተማሪዎ መፅሃፍ ውስጥ ያለውን ሥዕል ተማሪዎችን በቡድን እንዲሰሩ የሚከተሉትን ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማስቻል ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

1. ያልገባችሁን ጠያቄ ትጠይቃላችሁ ለሚለው አዎ የሚል ምልስ እንዲመልሱ መርዳት አስፈላጊ ነው፡፡
2. ጥቄ መመለስ መብት ወይስ ግዴታ የሚለውን መብት መሆኑን እንዲለዩ ማድረግ ይጠበቅቦታል

3. እጅ ሳያወጡ ጥያቄ መጠየቅ ትክክል እንዳልሆነ ተማሪዎችን ማስገንዘብ ከመምህራን ይጠበቃል

**ማስታወሻ**

**የተማሪዎች መብቶች ከሆኑት መካከል የተወሰኑት የሚከተሉት:**

- የመማር መብት
- ጥያቄ የመጠየቅ መብት
- መልስ የማግኘት መብት
- መፅሐፍ የማግኘት መብት እና ወዘተ፡፡

**ክትትል እና ግምገማ**

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

**የመማር ማስተማር ስልቶች**

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት

## ትምህርት .3: የተማሪዎች ግዴታ

(ክፍለግዜ: 3)

የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት፡-

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የተማሪዎችን መብቶች ይዘረዝራሉ፡፡

የዕለቱን ትምህርት ከመጀመርህ/ሽ በፊት ተማሪዎች በሰንደቃላማ ስነስረዓት ዙሪያ የተማሪዎችን ግንዛቤ ማዳበር ያስፈልጋል፡፡

ሥዕል፡ የሰንደቃላማ ስነስረዓት

የተማሪዎችን ግዴታ በሚለው ትምህርት ስር የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማዳበር እንዲረዳ ሥዕል ተዘጋጅቷል፡፡ ስለሆነም ይን ሥዕል በማብራራት ተማሪዎች እንዲረዱት ማድረግ ያስፈልጋለ፡፡

አፈ-ታሪክ-ኢፋ እና ፊኔት

የሠንደቅ አላማ ሥነስርአት አከባበር ኢፋ እና ፊኔት ወንድም እና እህት ናቸዉ:: ፊኔት የሠንደቅ አላማ ሥነስርዓትን በማክበር ትታወቃለች:: አንዳንዴም ከፊት በመሆን ባንድራ ትሰቅላለች:: ኢፋ ግን የሠንደቅ አላማ ስነስረዓት ሣያልቅ ወደ ክፍል ይሄዳል፡፡ በዚህ ባህሪዋ ፊኔት ምስጉን ስትሆን በትምህርቷ ከክፍሏ አንደኛ በመዉጣት ተሸላሚ ሆናለች፡፡ በሌላ መልኩ ኢፋ ግን ስነምግባር በመጣሱ ከትምህርት ቤት ተባረረ፡፡

ተግባር 4.4.

በተግባ 4.4. ስር የተቀመጠውን ጥያቄዎች ማሰራቶ በፊት ስለ ፌኔት እና ኢፉ አፈታሪክ ለተማሪዎች እንዲነበብ ማድረግ እሰፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ አፈታሪክ መሰረት ጥያቄዎቹን ተማሪዎች እንዲሰሩ መርዳት ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

ሥዕል፡ የተማሪ ዩኒፎርም መልበስ

የእለቱ ትምህርት ለማጠናከር እንዲረዳ ዩኒፎርም መልበስ አስፈለጊ መሆኑን የሚያሳይ ሥዕል ተዘጋጅቷል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የደንብ ልብስ የመልበስ ግዴታ እንዳለባቸው እና በንፅህና መያዝ እንዳለባቸው ማስረዳት ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

ተግባር 4.5.

በተማሪዎች መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ተግባር 4.5. ስር የተሰጠውን ጥያቄ የፌኔት እና ሮባን ባህሪ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በቡድን እንዲሰሩ መርዳት አስፈላጊ ነው፡፡ይህም ተማሪዎች የደንብ ልብሳቸውን በንፅህና በመያዝ መልበስ አስፈላጉ መሆኑን ማስገንዘብ የሁሉም መምህራን ግዴታ ነው፡፡

ሥዕል፡ እጅ በማውጣት ጥያቄ መጠየቅ

በተማሪዎች መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተቀመጠውን እጅ በማውጣት ጥያቄ መጠየቅ እንዳለባቸው የሚያሳየውን ሥዕል ተማሪዎች እንዲገነዘቡ ያድርጉ፡፡

ትረካ-መምርት ጃለኔ እና ተማሪ ኢፍቱ

መምህርት ጃለኔ ፊደል ሀን ማን ይጽፋል ብላ ጠየቀች? ኢፍቱ እጅ በማዉጣቷ እድል አግኝታ ወደ ፊት በመዉጣት ፍደል ሀን ጥቁር ሠሌዳ ላይ ፃፈች፡፡ ተማሪዎችም አጨበጨቡላት:: መምህርቷም ጉንጯን ሳመቻት:: ግዴታዋንም በመወጣትዋ በተማሪዎች እና በመምህራን ዘንድ የተከበረ እና የተወደደች ነች፡፡

ተግባር 4. 6.

በተግባር 4.6. ስር የተሰጠውን ጥያቄ ከማሰራትዋት በፊት የመምህርት ጃለኔ እና ተማሪ ኢፍቱ ምንባብ ለተማሪዎች አምብቡላቸው፡፡ እንዲሁም ሥዕሎችን በማስረዳት በምንባቡ ውስጥ ያለውን ባሪያት ተማሪዎች እንዲለዱት ማድረግ ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

ምንባብ፡ ሲምቦ እና ሶሬቲ የፈተና ሥነስርዓት

ሲምቦ እና ሶሬቲ እህትማማቾች ናቸዉ፡፡ የአንደኛ ክፍል ተማሪዎችም ናቸዉ፡፡ ሶረቲ እንቅልፉም ናት፡፡ በአንፃሩ ሲምቦ በጠዋቱ ከእንቅልፏ ትነሳለች፡፡ ሲምቦ ለፈተና እያጠናች ሲሆን ሶሬቲ ደግሞ ጫወታ ታዘወትራች:: ሲሚቦ እራሷን ችላ ፈተና ትሰራለች ሶሬቲ ደግሞ የፈተና መልስ ከጓደኛዋ ለማየት ትንጠራራለች በዚህ ምክኒያት መምህር አይቷት ከክፍል አስወጣት፡፡ ሲምቦ አንደኛ ወጥታ ስትሸለም' ሶሬቲ ግን ፈተና በመውደቁ ተናዳም እያለቀሰች ወደ ቤቷ ሄደች፡፡

ተግባር 4.7.

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተሰጠውን የተግባር ስራ የሲምቦ እና ሶሬቲ የፈተና ሥነስርዓት መሰረት በማድረግ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ማድረግ ከመህሩ የሚተበቅ ተግባር ነው፡፡

ትረካ፡ የግል ንፅህናን መጠበቅ

ዱሬቲ ንፅህናዋን የምትጠብቅ ልጅ ናት፡፡ ከሽንት ቤት ስትመለስ እጇቿን በሳሙና ትታጠባለች፤ ንፅህናዋን የምትጠብቅ ስለሆነ ጤነኛ ናት፡፡ ጤናማ በመሆኗም ደስተኛ ነች፡፡

ቡቤ ደግሞ ሽንት ቤት እያለ ሜዳ ላይ መጸዳዳት ይወዳል፡፡ ከተጸዳዳም ቡሃላ እጆቹን ስለማይታጠብ ሁል ጊዜ ይታመማል፡፡ በስተመጨረሻ ዱሬቲ ከክፍሏ አንደኛ በመዉጣት ስትሸለም ቡቤ ግን ታሞ ትምህርቱን አቋረጠ::

ተግባር 4.8.

1. ዱሬቲ ለምን ተሸለመች ለሚለው መልስ ከተነበበው ትረካ ላይ በመርኮዝ እንዲመልሱ ያድርጉ፡በተጨማሪም የዱሬቲን መልካም ባህሪ በመረዳት እንዲመልሱ መርዳት ከመምህሩ ይጠበቃል፡፡
2. ቡቤ ለም ታመመች ለሚለው ንፅህናዋን ስለማትጠብቅ ብለው እንዲመልሱ ማድረግ ያስፈልጋል

**ማስታወሻ የተማሪዎች ግዴታ:**

- መምህራኖችን ማክበር
- የትምህርት ቤቱን ንብረት በጥንቃቄ መጠቀም
- እጅ በማዉጣት ጥያቄ መመለስ
- ፈተናን በስነስርአት መስራት
- የግል ንፅህናን መጠበቅ
- የተማሪዎችን የመማሪያ መፅሐፍ በጥንቃቄ መጠቀም
- የክፍል እና የቤት ሥራን መስራት

## ትምህርት .4፡ መልካም ግንኙነት

(ክፍለግዜ: 4)

የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ክህሎት፤-

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የመልካም ግንኙነትአስፈላጊነትን ይገልፃሉ፡፡

ለጓደኛህ/ሽ ያለህን/ሽን ፍቅር እንዴት ትገልፃለህ የሚለውን የማነቃቂያ ጥያቄ ላይ ተማሪዎች በየተራ ሐሳባቸዉን እንዲሰጡ በማበረታታት የእለቱን ትምህርት ጀምር፡፡ በመቀጠል የመልካም ግንኙነት ምንነት ተማሪዎች ሊረዱት በሚችሉት ልክ ግንዛቤ ማስጨበጥ ይጠበቅብሃል/ሽ፡፡

ሥዕል፡ ጓደኛን ስለመውደድ

ጓደኛን ስለመውደድ የሚያሳይ ሥዕል ተማሪዎች አብረው በመብላት፤ በመረዳዳት እና በመተባበር የሚገለፅ መሆኑን ለማሣየት ስለሆነ ተማሪዎችን ማስረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

ተረት፡ ጓደኝነት

ዉሻ እና ድመት ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ አብረው  እየተጫወቱ ሳለ አንድ ቁርጥ ስጋ አገኙ:: ዉሻ ስጋዉን ለሁለት ከፍሎ ለድመት ሰጠ፡፡ ድመቷ ግን ያካፈልከኝ ስጋ ትንሽ ነዉ በማለት ጥል አስነሳች:: ከዚያ እንዲያስታርቃቸዉ ዝንጀሮን ለሽምግልና መረጡ፡፡ ዝንጀሮም እኩል አካፍላቹሃለሁ ብሎ ስጋዉን ተቀበላቸዉ፡፡ ሆኖም ዝንጀሮዉ ስጋዉ ስላስጎመጀዉ እኩል ላድርግላችሁ እያለ መግመጥ ጀመረ::ተራ በተራ ሲጎምጥ ስጋዉን ጨረሰ:: ዉሻ እና ድመትም ማልቀስ ጀመሩ::

ተግባር 4.9.

ከዚህ ተረት በመነሳት

1. ውሻው እና ድመቷ ለምን አለቀሱ ለሚለው እርስ በእርስ ባለመስማማታቸው፤ ጋደኝነታቸውን በጥቅም በመቀየራቸው
2. ውሻው እና ድመቷ ለምን ተፀፀቱ ለሚለው አተርፍ ብለው በማጉደላቸው
3. በምግብ ምክኒያት ከወንድም እህት ጋር ተጣልተህ ታውቃለህ ለሚለው ተረቱን ተሞርክዘው እንዲመልሱ ያድርጉ

ሥዕል፡ መልካምነት

መልካምነትን ለማስገንዘብ እንዲረዳ ታስቦ የተዘጋጀ ሥዕል ዙሪያ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስረዳት ከመምህሩ ይጠበቃል፡፡

አፈ-ታሪክ- እባብ ችና ሰው

በድሮ ጊዜ እባብ እና ሰዉ አብረው መንገድ ይሄዱ ነበር፡፡ እየተጓዙ ሳለ ትልቅ ወንዝጋ ይደርሳሉ በዚህን ጊዜ እባቡ ሰዉዬዉን ተሸከመህ አሻግረኝ ብሎ ለመነዉ፡፡ ሰዉዬዉም እባቡን በጭንቅላቱ ተሸክሞት ወንዙን አሻገረው ሆኖም ወንዙን ከተሻገሩ ቡሃላ እባቡ ከሰዉዬዉ አናት አልወርድም አለ፡፡ ከዚያ ለሽምግልና ጦጣ ጋር ሄዱ፡፡ጦጢትም ለሽምግልና ይመች ዘንድ ከሰውየው እራስ ላይ ውረድ አለችው፡፡ እባቡም ለሽምግልና ብሎ ከሰዉዬዉ እራስ ላይ ወረደ፡፡ በዚህን ጊዜ ጭልፊት እባቡን አይታ ወስዳዉ በላችው ይባላል፡፡

ተግባር 4.10

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ላይ የተቀመጠውን ጥያቄ ለመመለስ እንዲያመች ስለ እባቡ ችና ሰውዮው የተፃፈውን አፈታሪክ ያንብቡላቸው፡፡ በመቀጠልም

1. እባብን ታማኝ አለመሆኑ እንደጎዳው፤ ጭልፊት እንደወሰደችው እንዲገልፀ ያድርጉ
2. መልካምነት ጥቅም እንጂ ጉዳት እንደሌለው ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ሥዕል፡ ብልጠት

የብልጠትን አስፈላጊነት በተገቢው ለማስረዳት ይረዳ ዘንድ የተቀመጠውን ሥዕል ተማሪዎች እንዲረዱ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም ንስር እና ቀበሮ የተነገረውን አፈታሪክ ለተማሪዎቹ ያንብቡላቸው፡፡

አፈታሪክ- ንስር እና ቀበሮ

ከእለታት በአንዱ ቀን ንስር ዛፍ ላይ ተቀምጦ ስጋ ይበላ ነበር፡፡ ቀበሮ ደግሞ ዛፍ ስር ተቀምጣ ንስርን ወደ ላይ እያየች ስጋዉን የምታስጥልበትን ዘዴ አሰበች፡፡ ከዚያ መልክህ ያምራል ድምፅህ ግን አያምርም አለችዉ፡፡ ድምፅህ ቆንጆ ቢሆን ኖሮ ትዘፍናለህ አለችዉ፡፡ንስርም የሚያምር ድምፅ እንዳለዉ ለማሳየት ብሎ አፉን ከፍቶ ሲጮህ በአፉ ይዞ የነበረዉ ስጋ ወደቀ፡፡ ቀበሮዋም ፈጥና ስጋዉን ዋጠች ከዚያም አንተ ሞኝ ነህ ብላዉ ሄደች ይባላል፡፡

ተግባር 4.11.

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተጠየቀውን ጥያቄ ለማሰራት እንዲረዳንስር እና ቀበሮ የሚመለከት አፈታሪክ ለተማሪዎች በማንበብ ማሰራት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊነው፡፡

**ታማኝነት**

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተጠየቀውን መሬት ወድቆ ያገኛችሁትን እቃ ለባለቤቱ ትመልሳላችሁ የሚለውን የማነቃቂያ ተማሪዎችን በመጠየቅ እንዲመልሱ መርዳት ያስፈልጋል፡፡በተጨማሪም ተማሪዎች ስዕሉን እንዲረዱ መርዳት አስፈላጊ ነው፡፡

## መረዳዳት

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ መረዳዳትን የሚገልፁ ሥዕሎች ተቀምጠዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች እንዲረዱት በማድረግ ታላቅ ታናሹን ሲነከባከብ፤ ታናሽ ታላቁን ሲከብር ፤ ያላቸውን በመካፈል መደጋገፍ የመሳሰሉትን ግልፅ ማድረግ ውሳኝ ነው፡፡

ተግባር 4.12

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ በተለያየ ቦታ የተገለፁትን ሥዕሎች የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማስፋት ስለሚረዱ በደን ገላፃ በማድርግ የተሰጡትን የተለያዩ ጥያቄዎችን በቡድን እንዲሰሩ ማድረግ ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

መልካም ግንኙነትን የሚያስገነዝቡ ነጥቦችን ለማስገንዘብ ማስታወሻ መስጠት ስፈልጋል፡ለምሳሌ

- ✓ ጓደኛን መዉደድ
- ✓ መልካምነት
- ✓ ታማኝነት
- ✓ ጥንቃቄ ማድረግ
- ✓ መረዳዳት
- ✓ አንዱ የሌላዉን ሐሳብ መረዳት
- ✓ ብልጠት

## ትምህርት .5፡ መልካም ተሳትፎ

(ክፍለጊዜ: 4)

የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ክህሎት፤-

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የተሳትፎ አስፈላጊነት ያብራራሉ፡፡

ይህ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ጉዳዮች ዉስጥ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጋር የሚያያዝ ነዉ፡፡

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ክበባት ውስጥ የሚያደርጉት የነቃ ተሳትፎ ብዙ ጥቅሞች ያስገኝላቸዋል፡፡

**ሥዕል፡ መልካም ተሳትፎ**

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተቀመጡትን መልካም ተሳትፎን የሚያመለክቱ ሥዕሎችን በማብራራት የተማሪዎችን ግንዛቤ መጨመር ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ አካባቢን በማፅዳት ተግባር፤ እስፖት ክበብ እና የመሳሰሉት ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

**ሳትፎ ለተለያዩ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለምሳሌ፤**

- ለአካል/ሰዉነት ጥንካሬ
- ለአእምሮ ጥንካሬ
- ሐላፍነት መዉሰድ እና የመወጣት ስሜት ለማሳደግ
- በራስ የመተማመን ስሜት ለማጎልበት
- ልዩ ተሰጥዖ ለመጎናፀፍ እና ወዘተ የሚያካትት ነዉ፡፡

**በተማሪው መማሪያ ውስጥ ለተሰጠው አዛምድ ጥያቄ**

**መልስ-**

**1. መ 2. ሐ 3. ለ 4. ሀ**

## ክትትል እና ግምገማ

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

### የመማር ማስተማር ስልቶች

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

የምዕራፉ የማጠቃለያ-የክለሳ ጥያቄ_መልስ

| መልስ |
|---|
| 1. እዉነት 2. እዉነት3. እዉነት 4. እዉነት 5. እዉነት |

## ምዕራፍ 5. ባህል

**የተሰጠው ጊዜ: 20 ክፍለ ጊዜ**

### *የምዕራፉ መግቢያ*

ይህ ምዕራፍ አምስት አብይ የትምህርት ይዘቶች ያቀፈ ነው፡፡ እነሱም: ባህላዊ ምግብ፤ ባህላዊ አልባሳት፤ ባላዊ ጨዋታ፤ ባህላዊ እቃዎች እና ባህላዊ ስርዓቶች ናቸው፡፡ ለሁሉም የትምህርት ይዘቶች የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የትምርትይዘቱን ለማስገንዘብ እንዲረዳ አጫጭር ማስታወሻ እንዲሁም ስዕሎች ተካተዋል፡፡

በተጨማሪም በዚህ መምሪያ ውስጥ የመማር ማስተማር ስልቶች፤ የተማሪዎችን መረዳት የሚያግዙ ማስታወሻዎች፤. እንዲሁም ክትትል እና ግምገማዎች ተካተዋል፡፡

### የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የኦሮሞን ልዩ ልዩ ባህላዊ የምግብ አይነቶችን ያደንቃሉ፤
- የባህላዊ አልባሳት ምንነትን ያብራራሉ፤
- የአካባቢያቸውን ባህላዊ ጫወታዎች ይጫወታሉ፤
- የተለያዩ የባህላዊ እቃዎችን ይዘረዝራሉ፤
- የባህል ስርዓቶች ማክበር ፅንሰ ሃሳብ ይረዳሉ፡፡

## ትምህርት .1. ባህላዊ ምግብ

**የተሰጠው ሰዓት: 4 ክፍለ ጊዜ**

ከተማሪው የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት

ከዚህ ትምህርት ማጠቃለያ ቡኃላ ተማሪዎች፡

- የባህላዊ ምግብ ምንነትን ያብራራሉ፡፡

የእለቱን ትምህርት ከመጀመርህ/ሽ አስቀድሞ በተማሪው የመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ በተቀመጠው መሰረት የማነቃቂያ ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲመልሱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመቀጠል የሚከተሉትን ነጥቦች በማብራራት የእለቱን ትምህርት ማጠቃለል ከመምህር ይጠበቃል

ሥዕል፡ የተለያዩ የኦሮሞን ባህላዊ ምግች የሚያሳዩ ስዕሎችን ተማሪዎቹ እንዲለዩ ማድረግ አስፈላጊ ነው

ለምሳሌ፡

ገንፎ፤ ጭኮ፤ጨጨብሳ፤ጮሮርሳ የመሳሰሉትን የሚያሳይ መሆኑን ማብራራት ያፈልጋለ፡፡

- ኦሮሞ የራሱ የሆነ የምግብባህል አለው ::
- ባህላዊ ምግብ በባእላት ጊዜ ይዘጋጃል::
- ባህላዊ ምግብ ብዙን ጊዜ ለእንግዳ ነው የሚዘጋጀው፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

**የመማር ማስተማር ስልቶች**

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

ተግባር 5.1.

1. የተለያዩ ባላዊ ምግቦችን እንዲዘረዝሩ የሚረዳ ጥያቄ ተዘጋጅቶቷል፡፡ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ተማሪዎች እንዲሰሩ ያድርጉ

**ትምህርት . 2. የባህል አልባሳት**

**የተሰጠው ሰዓት: 4-ክፍለ ጊዜ**

የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት

ከዚህ ትምህርት ማጠቃለያ ቡኃላ ተማሪዎች፡

- ባህላዊ አልባሳት መች መች እንደሚለበስ ይገልፃሉ፡፡

የእለቱን ትምህርት ለመጀመር እንዲመች በተማሪው የመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ በተዘጋጀው የማነቃቂያ ጥያቄ መሰረት ተማሪዎች እንዲመልሱ እድል በመስጠት አሳታፊ በሆነ መንገድ የእለቱን ትምህርት ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመጨመር እንዲያመች የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

***ሥዕል፡ ባህላዊ አልባሳት***

በተማሪው የመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የተለያዩ የባህል አልባሳትን የሚያሳዩ ሥዕሎች ተካተዋል፡፡ በመሆኑም የተመሪዎችን ግንዛቤ ላማደራጀት እንዲረዳ ታስቡ ስለሆነ ገለፃ መስጠት ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር መሆኑን መምህራን መረዳት አለባቸው፡፡

ተግባር 5.2.

በተማሪው የመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የሚገኙትን ሥዕሎች ተማሪዎች እንዲገልጹ ማድረግ እስፈላጊ ነው፡፡

በተጨማሪም ለተማሪዎች ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ የሚከተሉትን ማስታወሻ ስጥ/ጪ

- ✓ ኦሮሞ የራሱ መገለጫ የባህል አልባሳት አለው፡፡
- ✓ የባህል አልባሳት በባዓላት ጊዜ ይለበሳል፡፡
- ✓ የባህል አልባሳት የማንነታችን መገለጫ ነው፡፡

## ትምህርት .3. ባህላዊ ጨዋታ

## የተሰጠው ሰዓት: 4-ክፍለ ጊዜ

ከተማሪው የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት

ከዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡

- የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችን ይዘረዝራሉ፡፡

በዚህ የትምህርት ክፍል ውስጥ የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመለካት የማነቃቂያ ጥያቄ ተማሪዎች እንዲመልሱ እድል በመስጠት የእለቱን ትምህርት መጀመር ይመከራል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን እውቀት ለማዳበር እንዲረዳ በተጨማሪ የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችን ለተማሪዎች ማስተማር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

### የመማር ማስተማር ስልቶች

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

ሥእል፡ ባህላዊ ጨዋታዎች

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ለመግለፅ እንዲረዳ የተለያዩ ጨዋታዎች ተዘርዝረዋል፡፡ እርሶም የተማሪዎችን ግንዘቤ ለመጨመር እንዲረዳ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

ተግባር 5.3.

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተዘረዘሩትን ባህላዊ ጨዋታዎች ተማሪዎች እንዲዘረዝሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የተሰጠውን ተግባር እንደ ሰሩ ማስቻል ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም የሚከተሉትን ማስታወሻ ሥጥ/ጪ

- ✓ ልጆች የተለያዩ ማህላዊ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡
- ✓ ጨዋታ ለልጆች መልካም ነው፡፡ ደስታን ይፈጥራል፡፡
- ✓ ልጆች ከጓደኞቻቸው ጋር ባህላዊ ጨዋታን ይጫወታሉ፡፡

## ትምህርት . 4. ባህላዊ እቃዎች

**የተሰጠው ሰዓት: 4-ክፍለ ጊዜ**

ከተማሪው የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት

ከዚህ ትምህርት ቡኃላ ተማሪዎች፡

- የባህላዊ እቃዎች አስፈላጊነትን ያብራራሉ፡፡

የእለቱን ትምህርት ከመጀመርህ/ሽ አስቀድሞ በተማሪው የመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ በተቀመጠው መሰረት የማነቃቂያ ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲመልሱ ማድረግ አሳታፊ በሆነ መልኩ መጀመር አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የባህላዊ እቃ አይነቶች እንዳሉ ተጨማሪ ማብራሪያ በመስጠት የተማሪዎችን እውቀት ማዳበር ይጠበቃል፡፡

ሥዕል፡ ባህላዊ እቃዎች

በተማሪው መፅሃፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ባህላዊ እቃዎች ለተማሪዎቹ በሚገባ መልኩ ማብራራት አስፈላጊ ነው፡፡ለምሳሌ ከእንጨት የተሰራ ትራስ፤ማንኪያ፤ሙቀጫ፤ወንበር የመሳሰሉትን ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ይህንን ሥዕል እንዲረዱ አደርግ/ጊ

ተግባር 5.4.

በተማሪው መፅሃፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ባህላዊ እቃዎች በተግባር 5.4. ስር በተጠየቀው መሰረት ተማሪዎች እንዲገልፁ ይርዱአቸው፡፡

በተጨማሪም የሚከተለውን ማስታወሻ ሥጥ/ጪ

- ✓ ኦሮሞ የተለያዩ የባህላዊ እቃ አይነቶች አሉት
- ✓ ባህላዊ እቃዎች ከተለያዩ ግብዓቶች ይዘጋጃሉ
- ✓ ባህላዊ እቃዎች ለመመገቢያነት ያገለግላሉ

## ክትትል እና ግምገማ

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

## የመማር ማስተማር ስልቶች

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

## ትምህርት .5 የባህል ስርዓቶች ማክበር

**የተሰጠው ሰዓት: 4-ክፍለ ጊዜ**

ከተማሪው የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት

ከዚህ ትምህርት ቡኃላ ተማሪዎች፡

- የባህል ስርዓቶች ማክበር አስፈላጊነት ያደንቃሉ፡፡

በተማሪ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የተጠቀሰውን የማነቃቂያ ጥያቄ መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማዳበር በሚረዳ መልኩ ማብራሪያ መስጠት ወሳኝ ነው፡፡ ለምሳሌ

- ✓ ኦሮሞ የኢሬቻን ባህል ያከብራል
- ✓ ኢሬቻ ፈጣሪ የሚለመንበት ቦታ ነው
- ✓ አባ ገዳዎች ክቡር ናቸው
- ✓ አባ ገዳን ማክበር ጥሩ ስነምግባር ነው
- ✓ ሃደ ሲንቄ ክብርት ነች
- ✓ ሃደ ሲንቄ መከበር አለባት

መልመጃ 5.1. አዛምድ

መልስ 1) ሠ 2) ሐ 3) መ 4)ሀ 5)ለ

**ክትትል እና ግምገማ**

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

**የመማር ማስተማር ስልቶች**

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

**የምዕራፍ ክለሳ ጥያቄዎች መልስ**

| **እውነት ወይም ሀሰት** |
|---|
| 1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት |
| **አዛምድ** |
| 1. ለ 2.መ 3. ሠ 4. ሐ 5.ሀ |

# ምዕራፍ 6. የማህበረሰብ እሴቶች

**የጠሰጠው ጊዜ: 20-ክፍለጊዜ**

***የምዕራፉ መግቢያ***

ይህ ምዕራፍ አምስት  አብይ የትምህርት ይዘቶች ያቀፈ ነው፡፡ እነሱም: መረዳዳት፤መደጋገፍ፤መዋድድእና መከባበር፤እንግዳ መቀበል እና ገጠር እና ከተማ ናቸው፡፡ ለሁሉም የትምህርት ይዘቶች የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የትምርትይዘቱን ለማስገንዘብ እንዲረዳ አጫጭር ማስታወሻ እንዲሁም ስዕሎች ተካተዋል፡፡

በተጨማሪም በዚህ መምሪያ ውስጥ የመማር ማስተማር ስልቶች፤ የተማሪዎችን መረዳት የሚያግዙ ማስታወሻዎች፤. እንዲሁም ክትትል እና ግምገማዎች ተካተዋል፡፡

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:**

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች:

- የመረዳዳትን ጥቅም ይዘረዝራሉ፤
- የመደጋገፍ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፤
- መዋደድን እና መከባበርን አስፈላጊነት ያደንቃሉ፤
- እንግዳ የመቀበል እሴትን ያሳያሉ፤
- የገጠር እና የከተማ የአኗኗር ዘዴን ይገልፃሉ፡፡

## ትምህርት . 1. መረዳዳት

## የተሰጠው ሰዓት፡ 4- ክፍለ ጊዜ

ከተማሪው የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት

ከዚህ ትምህርት ቡኃላ ተማሪዎች፡

- የመረዳዳት አስፈላጊነትን ይዘረዝራሉ፡፡

በተማሪ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የተጠቀሰውን ቤተሰብህን እንዴት ነው የምትረዳው የሚል የማነቃቂያ ጥያቄ መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በተጠየቀው ጥያቄ ላይ ሃሳብ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች በሰጡት ሃሳብ ላይ ማብራሪያ በመስጠት የተማሪዎችን እውቀት ማጎልበት የመምራን ዋና ተግባር ይሆናል፡፡

ትረካ፡ መረዳዳት

አቶ ሁንዴ እና ወይዘሮ ቶልቱ አ ርሶ አደሮች ናቸው፡፡ ኬና አንደኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን ሌሎ ደግሞ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ ነች፡፡  እኒህ ቤተሰብ በመረዳደት የሚሰሩ እና የማህበረሰቡን ችግር በመፍታት ይታወቃሉ ፡፡ አካባቢያቸውን በሳምንት አንዴ ያፀዳሉ፤ ቤታቸውን ደግሞ በየቀኑ ያፀዳሉ፡፡ በመሆኑም፣ ቤታቸው እና አካባቢያቸው ፅዱ ነው፡፡ ኬና እና ሌሎም መረዳዳትን ከቤተሰባቸው ተምረዋል፡፡ ሌሎ ወንድሟን ታስጠናዋለች፤ እሱም ያከብራታል፤ ምክሯን  ሁሉ ይቀበላል በተግባርም ያውላል፡፡ በዚህም ምክኒያት እሱም እንደ እህቱ በትምህርቱ ጎበዝ ነው፡፡በመሆኑም በጣም ይዋደዳሉ፡፡

ተግባር 6.1. መልስ

የአቶ ሁንዴ ቤተሰብ በመረዳዳት እና በመከባበራቸው በሰላም እና በደስታ  እንዲኖሩ አድርጓቸዋል፡፡ በመሆኑም የአቶ ሁንዴ ቤተሰብ በዚህ እሴታቸው በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ አረዓያ ይታያሉ ብለው እንዲመልሱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

## የመማር ማስተማር ስልቶች

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

## ትምህርት .2. መደጋገፍ

**የተሰጠው ሰዓት: 4 ክፍለ ጊዜ**

ከተማሪው የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት

ከዚህ ትምህርት ቡኃላ ተማሪዎች፡

- የመደጋገፍ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፡፡

በተማሪ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የተጠቀሰውን የማነቃቂያ ጥያቄ መሰረት በማድረግ ከተማሪዎች የተሰጠውን መልስ በማጠናከር የተማሪዎችን ግንዛቤ በሚያጠናክር መልኩ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን ግንዛቤ በተገቢው ለማጠናከር በሚረዳ መልኩ ተያያዥ ምሳሌዎችን መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 6.2.

የሚጠበቅ መልስ

መደጋገፍ የማህበረሰባችን አንዱ እሴት ሲሆን ሰዎች በችግር ጊዜ በሚያደርጉት መደጋገፍ ይገለፃል፡፡ ለምሳሌ፣ በእሳት የተያያዘ ቤትን ሰዎችን በማሳተፍ በማጥፋት መልሶ በመስራት የሚደረግን መደጋገፍ እንደ ምሳሌ በመጠቀም ማስተማር፡፡ በተጨማሪም በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ የተቀመጡትን ስዕላዊ መግለጫ በማብራራት የተማሪዎችን ግንዛቤ ማዳበር፡፡

**ማስታውሻ**

- ✓ የማህበረሰቡ የጋራ ስራዎች ላይ መሳተፍ አስፈላጊ ነው፡፡
- ✓ ተሳትፎ መልካም ልምድን ለማግኘት ይረዳል፡፡

## ትምህርት .3. መዋደድ እና መከባበር

**የተሰጠው ሰዓት: 4 ክፍለ ጊዜ**

ከተማሪው የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት

ከዚህ ትምህርት ማጠቃለያ ቡኃላ ተማሪዎች፡

- የመዋደድን አስፈላጊነት ያብራራሉ;
- የመከባበርን ጠቀሜታ ይገልፃሉ::

የመዋደድ እና የመከባበር አስፈላጊነትን ተማሪዎች በደንብ እንዲረዱ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተጠቀሰውን የማነቃቂያ ጥያቄ እንዲረዱ በማድረግ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ምሳሌዎችን በማጣቀሻነት በማቅረብ የተማሪዎችን ግንዛቤ መጨመር ከመምህራኖች ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ መርጃ መፅሃፍትን በማንበብ ማብራሪያ መስጠት ዋናው የመምህራን ስራ ነው፡፡

- ✓ እርስ በእርስ መዋደድ ከተማሪዎች የሚጠበቅ መልካም ስነምግባር ነው፡፡
- ✓ መከባበር እሴት ነው፡፡
- ✓ ተማሪዎች መዋደድ እና መከባበር አለባቸው፡፡

ተግባር 6.3.

ከተማሪዎች እንዲመልሱት የሚጠበቅ መልስ

በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ በተጠቀሰው መሰረት እንዴት አካል ጉዳተኛ የሆነን ተማሪ መውደድ እና ማክበር እንዳለባቸው በአግባቡ ማብራሪያ በመስጠት ማስተማር የመምህሩ ሃላፊነት ነው፡፡

### ክትትል እና ግምገማ

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

## የመማር ማስተማር ስልቶች

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት
- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

## ትምህርት .4. እንግዳ መቀበል

**የተሰጠው ሰዓት: 4 ክፍለ ጊዜ**

ከተማሪው የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት

ከዚህ ትምህርት ቡኃላ ተማሪዎች፡

- እንግዳ ተቀባይነትን ጠቀሜታ ይገልፃሉ

በዚህ የትምህርት ውስጥእንግዳን እንዴት ትቀበላላችሁ የሚል የማነቃቂያ ጥያቄ በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ተጠይቋል፡፡ በተጠየቀው የማነቃቂያ ጥያቄ መሰረት ተማሪዎች መልስ ለመስጠት ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ከመምህራን ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም, ተማሪዎች በሰጡት ሃሳብ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ በመስጠት የተማሪዎችን ግንዛቤ መጨመር አስፈላጊ ነው፡፡

ተግባር 6.4.

እንግዳን እንዴት መቀበል አለብን ከሚለው የተግባር ጥያቄ ላይ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

**ለምሳሌ እንግዳ መቀበያ መንገድ፡**

- ✓ ፀጉር በሌለው ቆዳ-ፈገግ ባለ ፊት
- ✓ ስጋ በሌለው አጥንት-በጥርስ በመሳቅ
- ✓ አጥንት በሌለው ስጋ-አነጋገር በማሳመር

የሚሉትን አባባሎች በመግለፅ የተማሪዎችን ግንዛቤ ማዳበር አስፈላጊ ተግባር ከመምህር ይጠበቃል፡፡

- እንግዳን መቀበል ጥሩ ስነ-ምግባር ነው፡፡
- እንግዳን ተነስተው ነው የሚቀበሉት
- እንግዳ ሲሳይ ነው፡፡

## ትምህርት . 5. የገጠር እና ከተማ የአኗኗር ሁኔታ

**የተሰጠው ሰዓት: 4 ክፍለ ጊዜ**

ከተማሪው የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ክህሎት

ከዚህ ትምህርት ቡኃላ ተማሪዎች፡

- የገጠር እና የከተማ የአኗኗር ሁኔታ ይገልፃሉ፡፡

በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ገጠር እና ከተማ በምን በምን ይታወቃሉ የሚል የማነቃቂያ ጥያቄን ለተማሪዎች በማቅረብ ተማሪዎች ሃሳባቸውን እንዲሰጡ በማድረግ የእለቱን ትምህርት መጀመር ውጤታማ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎች መልስን መሰረት በማድረግ በቂ የሆነ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊነው፡፡ ለምሳሌ፡

- የአካባቢያችን ማህበረሰብ ገጠር እና ከተማ ነው የሚኖረው፡፡ በገጠር እና በከተማ የሚኖሩ ማህበረሰቦች የራሳቸው የአኗኗር ሁኔታ አላቸው፡፡

ተግባር 6.5.

በተማሪ የመማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተቀመጠውን ስዕላዊ መግለጫ ተማሪዎች በሚረዱት አግባብ ማስረዳት የመምህራን ግዴታ መሆኑን መገንዘብ እንደ መምህር አስፈላጊ ነው፡፡

### ክትትል እና ግምገማ

- ✓ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ✓ በተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ማስገንዘብ
- ✓ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ተማሪዎችን መስገንዘብ

### የመማር ማስተማር ስልቶች

- ✓ የእለቱን ትምህርት በማነቃቂያ ጥያቄ መጀመር
- ✓ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሰራት

- ✓ አጫጭር ማስታወሻ መስጠት
- ✓ በቡድን ተማሪዎችን ማሰራት

**የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄ መልስ**

| |
|---|
| **የእውነት ወይም ሀሰት መልስ** |
| 1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት 5. እውነት |
| **የምርጫ መልስ** |
| 6. መ 7. መ 8. ሀ |
| |

# የ1ኛ ክፍል የግበረገብ ትምህርት ሲለበስ

## ምዕራፍ 1፡ መልካም ስነምግባር (የተሰጠው ሰዓት፡ 20 )

### የመማር ውጤቶች፡

ከዚህ ምዕራፍ ማጠናቀቂያ በሃላ ተማሪዎች፡

- ✓ የልጆች ስነምግባር ምንነት መረዳት፤
- ✓ የስነምግባር ጥቅሞችን ማብራራት፤
- ✓ ከጎጂ ድርጊቶች መጠንቀቅ፤
- ✓ ከስነምግባር ጉድለት የሚመጡ ጉዳቶች መጠንቀቅ

| ብቃት | ይዘት | መማር ማስተማር ስልት | ግምገማና ክትትል |
|---|---|---|---|
| ✓ መልካም ስጀምግባር በግለፅ<br>✓ የልጆችን ስነምግባር ማብራራት<br>✓ የመልካም ስነምግባር አስፈላጊነት ማወቅ<br>✓ ከጎጂ ድርጊቶች መጠበቅ አስፈላጊነትን ይለያሉ<br>✓ ከስነምግባር ጉድለቶች የሚመጡትን ጉዳቶች ይለያሉ | 1. መልካም ስነምግባር<br>1.1. የልጆች ስነምግባር<br>1.2. የስነምግባር ጠቀሜታ<br>1.3. ከጎጂ ድርጊቶች መጠበቅ<br>1.4. ከስነምግባር ጉድለቶች የሚመጡትን ጉዳቶች | ✓ የማነቃቂያ ጥያቄን መጠየቅ<br>✓ በቡድን ተግባራትን ማሰራት<br>✓ የተለያዩ ሥዕሎችን፤ መልመጃዎችን እንዲሁም ተግባራትን ተማሪዎችን ማሰራት<br>✓ ለይዘቶቹ በሚስማማ መልኩ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ማስተማር<br>✓ የተለያዩ አፈታሪኮችን፤ ተረቶችን፤ ምንባቦችን ማሰራት | ✓ የተማሪዎችን የመመር ሁኔታ መከታተል<br>✓ ለውጦችን በመመዝገብ ከተቀመጠው ብቃት ጋር መገምገም<br>✓ ሁል ጊዜ ጥሩ የሆነ ገንቢ ሃሳብ መስጠት<br>✓ ተግባራትን ተማሪዎችን በማሰራት መገምገም |

## ምዕራፍ 2 ፡ ቤተሰብ እና የልጆች ስነምግባር (የተሰጠው ሰዓት፡ 19)

### የመማር ውጤቶች፡

ከዚህ ምዕራፍ ማጠናቀቂያ በሃላ ተማሪዎ:

- ቤተሰብ እና የልጆት ስነምግባር መለየት፤
- የቤተሰብ አባላትን መዘርዘር፤
- የቤተሰብ አባለትን ድርሻ መግለፅ፤
- የቤተሰብን እሴትን ማድነቅ፡፡

| ክህሎት | ይዘት | መማር ማስተማር ስልት | ግምገማ እና ክትትል |
|---|---|---|---|
| ✓ ቤተሰብ እና ድርሻቸውን መለየት<br>✓ የቤተሰብ አባላትን ድርሻ መለየት<br>✓ የቤተሰብ አባላትን እሴት መadenqe | 2. ቤተሰብ እና የልጆች ስነምግባር<br>2.1. የቤተሰብ አባላት<br>2.2. የቤተሰብ አባላት ድርሻ<br>2.3. የቤተሰብ እሴቶች | ✓ የማነቃቂያ ጥያቄን መጠየቅ<br>✓ በቡድን ተግባራትን ማሰራት<br>✓ የተለያዩ ሥዕሎችን፤ መልመጃዎችን እንዲሁም ተግባራትን ተማሪዎችን ማሰራት | ✓ የተማሪዎችን የመመር ሁኔታ መከታተል<br>✓ ለውጦችን በመመዝገብ ከተቀመጠው ብቃት ጋር መገምገም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ✓ ለይዘቶቹ በሚስማማ መልኩ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ማስተማር<br>✓ የተለያዩ አፈታሪኮችን፤ ተረቶችን፤ ምንባቦችን ማሰራት | ✓ ሁል ጊዜ ጥሩ የሆነ ገንቢ ሃሳብ መስጠት<br>✓ ተግባራትን ተማሪዎችን በማሰራት መገምገም |

ምዕራፍ 3: ጉርብትና ( የተሰጠ ክፍለ ጊዜ:19)

**የመማር ውጤቶች:**

ከዚህ ምዕራፍ ማጠናቀቂያ ቡሃላ ተማሪዎ:

- ✓ የጉርብትና ባህርያትን መግለፅ፤
- ✓ የመልካም ጉርብትና አስፈላጊነት ማብራራት፤
- ✓ ጉርብትናን የሚያጠናክሩ ድርጊቶች ይዘረዝራሉ::

| ክህሎት | ይዘት | መማር ማስተማር ስልት | ግምገማ እና ክትትል |
|---|---|---|---|
| ✓ የጉርብትና ምንነትን ይጠቅሳሉ<br>✓ የመልካም ጉርብትና አስፈላጊነትን ያብራራሉ<br>✓ ጉርብትናን ያደንቃሉ<br>✓ ጉርብትናን የሚያጠናክሩ ድርጊቶች መተንተን | 3. የጉርብትና<br>3.1. ጎረቤት<br>3.2. የመልካም ጉርብትና አስፈላጊነት<br>3.3. ጉርብትናን የሚያጠናክሩ ድርጊቶች | ✓ የማነቃቂያ ጥያቄን መጠየቅ<br>✓ በቡድን ተግባራትን ማሰራት<br>✓ የተለያዩ ሥዕሎችን፤ መልመጃዎችን እንዲሁም ተግባራትን ተማሪዎችን ማሰራት<br>✓ ለይዘቶቹ በሚስማማ መልኩ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል | ✓ የተማሪዎችን የመመር ሁኔታ መከታተል<br>✓ ለውጦችን በመመዝገብ ከተቀመጠው ብቃት ጋር መገምገም<br>✓ ሁል ጊዜ ጥሩ የሆነ ገንቢ ሃሳብ መስጠት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ማስተማር<br>✓ የተለያዩ አፈታሪኮችን፤ ተረቶችን፤ ምንባቦችን ማሰራት | ✓ ተግባራትን ተማሪዎችን በማሰራት መገምገም |

# ምዕራፍ 4፡ የተማሪዎች ስነምግባር ( የተሰጠው ሰዓት፡ 19)

## የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የተማሪዎች ሥነምግባር  ምንነት መግለፅ፤
- የመምህራን መዝሙር፤
- መምህራኖችን ማክበር፤
- የተማሪዎች መብት እና ግዴታ መዘርዘር፤
- የመልካም ግንኙነት ጥቅምን መግለፅ፡፡
- የተሳትፎን አስፈላጊነት ይረዳሉ፡፡

| ክህሎት | ይዘት | መማር ማስተማር ስልት | ግምገማ እና ክትትል |
|---|---|---|---|
| ✓ የመምህራን መዝሙር አስፈላጊነት መዘመር<br>✓ የተማሪዎችን መብት መተግበር<br>✓ የተማሪዎችን ግዴታ መተግበር | 4. የተማሪዎች ስነምግባር<br>4.1.የመምህራን መዝሙር<br>4.2. የተማሪዎችን መብት<br>4.3. የተማሪዎችን ግዴታ | ✓ የማነቃቂያ  ጥያቄን  መጠየቅ<br>✓ በቡድን ተግባራትን ማሰራት<br>✓ የተለያዩ ሥዕሎችን፤ መልመጃዎችን እንዲሁም | ✓ የተማሪዎችን የመመር ሁኔታ መከታተል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ✓ የመልካም ግንኙነት መለየት<br>✓ የመልካም ተሳትፎ አስፈላጊነትን መግለፅ | 4.4. መልካም ግንኙነት<br>4.5. መልካም ተሳትፎ | ተግባራትን ተማሪዎችን ማሰራት<br>✓ ለይዘቶቹ በሚስማማ መልኩ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ማስተማር<br>✓ የተለያዩ አፈታሪኮችን፤ ተረቶችን፤ ምንባቦችን ማሰራት | ✓ ለውጦችን በመመዝገብ ከተቀመጠው ብቃት ጋር መገምገም<br>✓ ሁል ጊዜ ጥሩ የሆነ ገንቢ ሃሳብ መስጠት<br>✓ ተግባራትን ተማሪዎችን በማሰራት መገምገም |

## ምዕራፍ 5. ባህል (የተሰጠው ጊዜ: 20 ክፍለ ጊዜ)

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:**

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ተማሪዎች:-

- ✓ የኦሮሞን ልዩ ልዩ ባህላዊ የምግብ አይነቶችን ያደንቃሉ፤
- ✓ የባህላዊ አልባሳት ምንነትን ያብራራሉ፤
- ✓ የአካባቢያቸውን ባህላዊ ጫወታዎች ይጫወታሉ፤
- ✓ የተለያዩ የባህላዊ እቃዎችን ይዘረዝራሉ፤
- ✓ የባህል ስርዓቶች ማክበር ፅንሰ ሃሳብ ይረዳሉ።

| ክህሎት | ይዘት | መማር ማስተማር ስልት | ግምገማ እና ክትትል |
|---|---|---|---|
| ✓ የባህላዊ የምግብምንነትን መግለፅ<br>✓ የባህላዊ አላባሳት ምንነትን ያደንቃሉ<br>✓ ባህላዊ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ<br>✓ ባህላዊ እቃዎችን ይዘረዝራሉ<br>✓ ባህላዊ እሴቶችን ይለያሉ | 5. ባህል<br>5.1.ባህላዊ የምግብ<br>5.2. ባህላዊ አልባሳት<br>5.3. ባህላዊ ጫወታዎች<br>5.4. ባህላዊ እቃዎች | ✓ የማነቃቂያ ጥያቄን መጠየቅ<br>✓ በቡድን ተግባራትን ማሰራት<br>✓ የተለያዩ ሥዕሎችን፤ መልመጃዎችን እንዲሁም ተግባራትን ተማሪዎችን ማሰራት | ✓ የተማሪዎችን የመመር ሁኔታ መከታተል<br>✓ ለውጦችን በመመዝገብ ከተቀመጠው ብቃት ጋር መገምገም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 5.5. ባህላዊ ስርዓቶች | ✓ ለይዘቶቹ በሚስማማ መልኩ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ማስተማር<br>✓ የተለያዩ አፈታሪኮችን፤ ተረቶችን፤ ምንባቦችን ማሰራት | ✓ ሁል ጊዜ ጥሩ የሆነ ገንቢ ሃሳብ መስጠት<br>✓ ተግባራትን ተማሪዎችን በማሰራት መገምገም |

## ምዕራፍ 6. የማህበረሰብ  እሴቶች (የጠሰጠው ጊዜ: 20-ክፍለጊዜ)

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:  በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች:**

- የመረዳዳትን ጥቅም ይዘረዝራሉ፤
- የመደጋገፍ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፤
- መዋደድን እና መከባበርን አስፈላጊነት ያደንቃሉ፤
- እንግዳ የመቀበል እሴትን ያሳያሉ፤
- የገጠር እና የከተማ የአኗኗር ዘዴን ይገልፃሉ፡፡

| ክህሎት | ይዘት | መማር ማስተማር ስልት | ግምገማ እና ክትትል |
|---|---|---|---|
| ✓ የመረዳዳትን ጥቅም ፅንሰ ሃሳብ መረዳት<br>✓ የመደጋገፍ አስፈላጊነትመለየት<br>✓ መዋደድን እና መከባበርን አስፈላጊነት ይገልፃሉ<br>✓ እንግዳ የመቀበል እሴትን ያሳያሉ፤<br>✓ የገጠር እና የከተማ የአኗኗር መግለፅ | 6. የማህበረሰብ እሴቶች የመደጋገፍ<br>6.1. መዋደድን እና መከባበርን<br>6.2. እንግዳ የመቀበል<br>6.3. የገጠር እና የከተማ የአኗኗር | ✓ የማነቃቂያ ጥያቄን መጠየቅ<br>✓ በቡድን ተግባራትን ማሰራት<br>✓ የተለያዩ ሥዕሎችን፤ መልመጃዎችን እንዲሁም ተግባራትን ተማሪዎችን ማሰራት<br>✓ ለይዘቶቹ በሚስማማ መልኩ ተማሪዎችን በቡድን | ✓ የተማሪዎችን የመመር ሁኔታ መከታተል<br>✓ ለውጦችን በመመዝገብ ከተቀመጠው ብቃት ጋር መገምገም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በመከፋፈል ማስተማር<br>✓ የተለያዩ አፈታሪኮችን፤ ተረቶችን፤ ምንባቦችን ማሰራት | ✓ ሁል ጊዜ ጥሩ የሆነ ገንቢ ሃሳብ መስጠት<br>✓ ተግባራትን ተማሪዎችን በማሰራት መገምገም |